Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
SEEK WISDOM, ELEVATE YOUR INTELLECT AND SERVE HUMANITY !

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም  የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ  ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ፤ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ስናፍቅሽ አዱኛ

መስከረም 2016ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ፤ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝም የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ  ስነጽሁፍና ፎክረሎር ክፍል ትምህርት


በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት

የቀረበ ጥናት


በ

ስናፍቅሽ አዱኛ ባይሳ

አማካሪ

ጌታሁን አማረ(ፐ/ር)



መስከረም 2016ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## አዲስ አበባ፡ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም  የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ  ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

# በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ፤ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ስናፍቅሽ አዱኛ ባይሳ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ______________________________ፊርማ ______________

የውስጥ ፈታኝ ስም__________________________ፊርማ______________

የውጪ ፈታኝ ስም__________________________ፊርማ_______________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ደረጃ እንድበቃ ላደረገኝ  ለዕውቀት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር በነገሮች ሁሉ አመሰግነዋለሁ፡፡

በመቀጠል ይህ ጥናት ከርዕስ አመራረጥ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመለገስ ፣ስህተቴን በማረም ና ምላሽ በመስጠት ጊዜያቸውን ሳይሰስቱ  ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ  እንዲይዝ ለረዱኝ መምህሬና አማካሪዬ ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

በመጨረሻም ለስራዬ መሳካት ሲደግፉኝና  ሲያበረታቱኝ ለነበሩ ቤተሰቦቼ ፤በተለይም በብዙ ነገር ከጎኔ በመሆን አጋርነታቸውን ላሳዩኝ አለም አሰፋ ፣ ዘላለም ዘውዴ ፣ጂኔኑስ ዘላለም ፣ሂሪያ ዘላለም ምስጋናዬ ከልብ ነው ፡፡

# የይዘት ማውጫ

ገጽ


ምስጋና ..... i

የሰንጠርዥ ማውጫ ..... iv

አጠቃሎ ..... v

ምዕራፍ አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..... 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ..... 4

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 4

1.5 የጥናቱ ወሰን ..... 5

ምዕራፍ ሁለት ..... 6

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ..... 6

2.1 የንባብ ምንነት ..... 6

2.2 የማንበብ ተነሳሽነት ..... 7

2.3 አንብቦ መረዳት ምንነት ..... 9

2.4. የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት ..... 10

2.5 የንባብ ትምህርት አላማ ..... 11

2.6 የንባብ ስልቶች ..... 11

2.7 የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ..... 13

2.8 አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን ..... 14

2.8.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና ..... 14

2.9 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች ..... 15

2.10. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... 17

ምዕራፍ ሦስት ..... 21

የአጠናን ዘዴ ..... 21

3.1 የናሙና አመራረጥ ..... 21

3.1.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ..... 21

3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ ..... 21

3.1.3 የመምህራን አመራረጥ ........ 22
3.2 መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 22
3.2.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመዘን የሚሰጥ ፈተና ........ 22
3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 23
3.2.3 ቃለ መጠየቅ ........ 24
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 24
ምዕራፍ አራት ........ 26
የመረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 26
4.1.አንብቦ መረዳት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 26
4.2 የአጠቃላይ ተፈታኞች አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና ........ 27
4.3 ከፅሁፍ መጠይቅ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃዎች ትንተና ........ 31
ምዕራፍ አምስት ........ 41
ማጠቃለያና አስተያየት ........ 41
5.1 ማጠቃለያ ........ 41
5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 43
ዋቢ ጽሁፎች ........ 44
አባሪዎች ........ 48

# የሰንጠርዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ........ 17

ሠንጠረዥ 2፡ በአራሚ 1 እና 2 ለተጠኚዎች ከቀረቡ አንብቦ የመረዳት መለኪያ ሁለት ፈተናዎች የተጠኚዎች አጠቃላይ እና የአማካይ ውጤት ድግግሞሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ........ 27

ሠንጠረዥ 3፡ የፈተና አንድ እና ሁለት ነጠላና አጠቃላይ አማካይ ........ 29

ሠንጠረዥ 4፡ በሁለት አራሚዎች የተገኘ በምድብ የተጠቃለለ የተፈታኞች አንብቦ የመረዳት ፈተና አጠቃላይ አማካይ ውጤት ........ 30

ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኚዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ........ 31

ሠንጠረዥ 6፡ የተጠኚዎችን በአማርኛ የቀረቡ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ ........ 34

ሠንጠረዥ 7፡ የተጠኚዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ ከቀርቡት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃዎች ........ 37

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አብይ  አላማ  አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ  የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በነጌሌ ቦረና ከተማ  ከሚገኙ የመንግስት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት በተመረጠው አንድ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው።ጥናቱን ለማካሄድ በጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም ለተማሪዎች የሚሰጠው የአንብቦ መረዳት ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ ለመምህሯ የቀረበ ቃለ መጠይቅ ናቸው። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች በጥናቱ ተተንትነው ቀርበዋል። በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱት ተማሪዎች በአማርኛ የቀረቡት ጽሁፎችን የማንበብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል ። ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ከሚጠቀሱት ውስጥ የንባብ ትምህርት አሰጣጥና የመማሪያ መጽሐፍት ይጠቀሳሉ ። ከመጠይቁ በተገኘው መረጃም ንባብን ከማስተማሩና ከመማሪያ መጽሐፍት አኳያ ችግሮች እንዳሉ ነው ።  በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት  ተማሪዎችን እደማያሳትፉ ማለትም አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩን የሚከናወን በመሆኑ ተማሪዎች በቂ ልምምድ አለማድረጋቸውን ይገልጻሉ። የመማሪያ መጽሐፉም በበቂ ሁኔታ ለተማሪዎቹ አለመድረሱ እንደዚሁም የተማሪዎችም የንባብ ተነሳሽነት ከማጎልበት አንጻር ያለው አስተዋጽኦ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል ። በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያግዛሉ ተብለው በአጥኚዋ የቀረቡ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች እና በየደረጃው በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጸሐፍት ውስጥ ከሰፈሩት ዓላማዎች መካከል አንዱ የቋንቋውን የክሂል ዘርፎች ማዳበር ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ደግሞ በተማሪው ዘንድ እንዲዳብሩ ከሚጠበቁ ዋና ዋና የክሂል ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የትምህርት ዘርፎች በአግባቡ ለመገንዘብ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው (Dubin 1989፣Nuttall 1982፣ Dubin and David 1991) ፡፡

ዘውዱ (1998፡1) Tonjes (1991:7)ን ጠቅሰው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው አራት መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ የማንበብ ክሂል ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ ክሂል በተግባቦት ሂደትም ሆነ በትምህርት ህይወት ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል አይነተኛ መሳሪያ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

Brown (1994) እንደገለፁት ማንበብ በአብዛኛው ከትምህርት ቤት ውጪ የሚለመድ ክሂል አይደለም፡፡ሰዎች ማንበብን የሚማሩት እና የሚያዳብሩት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድና በመለማመድ ነው ስለሆነም ቋንቋ በሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የማንበብ ትምህርት ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ክሂል መሆኑን Brown(1994) ሲገልፁ በተጨማሪም Patirica and Pamela (2004) በትምህርት ቤት ከሚቀርቡ የእውቀትና የክሂል ዘርፎች የንባብ ትምህርት ትልቁን ድርሻ እንዲይዝ መደረጉን ያብራራሉ፡፡

ንባብን ለተለያዩ ተግባራት እንጠቀምበታለን፡፡ በተለያዩ ምሁራን የተከናወኑ ጥናቶችን በማንበብ እውቀታችንን እናሰፋበታለን፡፡የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን በማንበብ ደስታችንንም ሆነ ሀዘናችንን እየተወጣን ጊዜያችንን እናሳልፍበታለን፡፡በተጨማሪም በጋዜጦችና በመፅሔቶች አማካኝነት በዓለም ውስጥ የተከናወኑትን አዳዲስ ክስተቶችን እንረዳበታለን፡፡በአጠቃላይ ንባብ ሊሰጠው የሚችለውን ጠቀሜታ Nuttall (1996፡3) ሲያጠቃልሉት እንዲህ በማለት ነው፡፡« ታነባለህ ምክንያቱም ከምታነበው

ነገር አንድ ነገር ለመውሰድ ትፈልጋለህ፤ ከምታነበው ነገር እውቀትን፣ሀሳብንና መዝናናትን ትፈልጋለህ፤ የሆነው ሆኖ የምታነበው ከፅሁፍ ውስጥ አንድ የምትፈልገውን ነገር ለመውሰድ ነው፡፡» ይህን አገላለፅ Browns (1994:285), Grelle (1981:5) እና ሌሎችም ይስማሙበታል፡፡

ንባብ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ እንደ አንድ ዘርፍ ሆኖ በትምህርት ቤት መርሃ-ትምህርት ተነድፎለት መሰጠት ያለበት መሆኑ አያጠራጥርም ፤እንዲያውም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ የሌሎችን ትምህርቶች ማስተማሪያ ቋንቋ ከሆነ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ሁሉ ለንባብ ትምህርት የተለየ ትኩረት መስጠት እንደሚገባን Carrell-Devine and Eskey (1988:1) ጠቁመዋል፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከተሰነዘሩት ሀሳቦች የምንረዳው ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትንም ሆነ ሌሎች ለትምህርቱ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ፅሁፎችን በሚገባ አንብበው ለመገንዘብ ይችሉ ዘንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲዳብር ለክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን እንዲሁም አንብቦ መረዳት በተማሪዎች ዘንድ እንዲዳብሩ ከሚጠበቁ የክሂል ዘርፎች አንዱና ዋናው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ክሂል የሚሰጠው ትኩረት ከሌሎቹ ክሂሎች አንጻር ሲታይ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ከሚቀርቡት ልዩ ልዩ መልመጃዎች መካከል ትልቁን ድርሻ የሚያዙትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ናቸው (በየነ 1986)፡፡ ይሁን እንጂ በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከክፍል ደረጃቸው አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን በተደጋጋሚ የሚገልጹት ጉዳይ ነው (ተስፋዬ 1986)፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት በተለያዩ በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የተካሄዱ ጥናቶችም የሚያረጋግጡት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው(አስቴር 2010፣ ሒሩት 2008፣ እንድሪስ 2009፣ ዘውዱ 2008)፡፡

ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ለመመርመር በነጌሌ ቦረና ከተማ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን መፈተሽ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው፡፡ ጥናቱ በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ እንዲያተኩር የተፈለገበት ምክንያት ተማሪዎች በ7ኛ ክፍል ትምህርታቸው ላይ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ

እንደሚገኝ ለመገምገም እንዲያስችል በማሰብ ነው፡፡ በዚህም ከክፍል ደረጃቸው አንፃር የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለበትን ደረጃ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም ለዚህ አስተዋፅኦ ያደረጉ አበይት ምክንያቶችንም ለይቶ ለማሳየት ጥረት ያደርጋል፡፡

ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግም አጥኚዋ በመረጠችው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ አራት ቀደም ጥናቶችን አይታለች፡፡እነዚህም አስቴር 2010፣ ሒሩት (2008)፣እንድሪስ 2009 እና ዘውዱ (2008) ሲሆኑ ቀደምት ጥናቶቹ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጹሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ እና ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያነት በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ የተኮሩና በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡እነዚህም ጥናቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የፈተሹ ሲሆኑ ሁሉም በጥናታቸው ውጤት የተማሪው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለከቱ ናቸው፡፡

በመሆኑም  የቀደምት ጥናቶቹ ዝርዝር ማብራሪያ በምዕረፍ ሁለት ላይ በስፋት የሚቀርብ ይሆናል፡፡ይሁን እንጂ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ብቻ ለይቶ በአማርኛ የተጻፉ ፅሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ይሁነኝ ብሎ ጥናት በማድረግ ያረጋገጠ አላጋጠመኝም፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ማንበብ በማንኛውም የትምህርት መስክ ስኬታማ ለመሆን ጠቃሚና ወሳኝ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናቷን እንድታካሄድ ካነሳስዋት ዋናው ምክንያት የማንበብ ተነሳሽነተና አንብቦ መረዳት በመማር ሂደትም ሆነ አጠቃላይ በህይወት መስክ አዳዲስ እውቀቶችን ማግኛ ግንዛቤን ማበልጸጊያ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ስለሆነም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  የተፃፉ ፅሁፎችን የማንበብ ተነሳሽነትና  አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ይህን ጥናት ማድረግ አስፈልጓል፡፡የዚህ ጥናት አላማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል  በምስራቅ ቦረና  ዞን ነጌሌ ቦረና ከተማ በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ለመፈተሽ አላማ ይዛ ተነስታለች፡፡ ይህም ተማሪዎች አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸው ላይ ለደረጃው ከሚጠበቀው ችሎታ አንጻር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ

እንደሚገኝ ለመፈተሽ እንዲሁም የመፍትሔ ሀሳብ ለመሰንዘር ያስችላል በሚል ተነሳሽነት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር፤
2. የተማሪዎቹን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መፈተሽ፤
3. ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውን ለማዳበር ያላቸውን የንባብ ፍላጎት መመርመር፣

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. ጥናቱ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማስገኘት የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርል፡፡
2. አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችን ለማያስተምሩ መምህራን የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተገንዝበው የማስተማር ስልታቸውን ለማሻሻል የሚረዳቸውን ሀሳብ እንዲያገኙ ያግዛል
3. ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሻሻል ይችሉ ዘንድ ማከናወን ያለባቸውን ተግባራት ይጠቁማል፡፡
4. የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ጋር በተያያዘ መልኩ ወደፊት ለሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከትምህርት ቤት አንፃር ያተኮረው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን በነጌሌ ቦረና ከተማ ከሚገኙ ስምንት አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል በሾላ 1ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በነጌሌ ቦረና ከተማ ከሚገኙ ስምንት የመንግስት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች የሚማሩበት እና ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጥበት መሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም ጥናቱ በ2015 ዓ.ም በ7ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙትና አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ደረጃ፣ የንባብ ትምህርት ሞጁሎች ተተግባሪነት እና ሌሎች የንባብ ክሂል ዘርፎችን በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የሚገኙ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ተካተዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የንባብ ምንነት፣ የንባብ ተነሳሽነት ፣የአንብቦ መረዳት ምንነት፣ የማንበብ ትምህርት አስፈላጊነት፣የንባብ ትምህርት ዓላማ ፣የንባብ ስልቶች ፣የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃ ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን ፣አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 2.1 የንባብ ምንነት

ንባብን በአንድ ቃል መግለፅ እንደማይቻል ምሁራን ይናገራሉ፡፡ስለሆነም ንባብ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያየ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ Davies (1995:1) ‹‹ንባብ ግላዊ ነው፡፡ ንባብ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን የአንድ ፀሐፊ መልዕክት በመከተል ምላሽ በመስጠት የምንሞክርበት አእምሮአዊ ተግባር ነው፡፡ ግላዊ ተግባር ስለሆነ የአነባበቡን ሂደትና ለፀሐፊውም የሚሰጠውን ምላሽ በቀጥታ ልናስተውል እንችላለን›› ይላሉ፡፡ ከዚህም ንባብ አንድ ሰው በግሉ የሚያካሂደውና አእምሮአዊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን፡፡

ንባብ ከቋንቋ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ እንደ Harmer (1991:17-18), Sheng (2000:12) ገለፃ ንባብ ከመቀበያ ክሂሎች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ከምናነበው ፅሁፍ ውስጥ ፍሬ ነገሩን ነቅሶ ሰማውጣትን፣የምንባቡን ዝርዝር ሀሳብ መረዳትን፣ መቀበልና ማስተላለፍን፣የቃላት አውዳዊ ፍቺ መረዳትን ወዘተ አጠቃሎ የያዘ መሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ንባብ ፀሐፊ በፅሁፉ ውስጥ የሚያስተላልፈውን መልዕክት አንብቦ ለመረዳት የሚከውን ተግባር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

እንዲሁም Grellet (1981:8) “ንባብ ማለት መገመት፣መተንበይ፣ማመሳከርና ራስን ጥያቄ መጠየቅ የሚሉትን የሚያጠቃልል ንቁ ተሳትፎ የሚያሻው ሂደት ነው”፡፡ ከዚህም ንባብ አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺዎች የሚገምትበት ገና ከመነሻው ባገኘነው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘት ወደ ፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ የሚያነበውን ጽሁፍ መረዳትና አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት

መሆኑን እንረዳለን፡፡በሌላም በኩል የተለያዩ ምንባቦችን ቢያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶች መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡

Nuattall (2000) ንባብ ጸሐፊውን በስራው ውስጥ ያሰፈረውን ቁም ነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ተደራሲው በንባብ ሂደት የፅሁፉን ፍሬ ሀሳብ ለመገንዘብ አስፈላጊ መረጃን ከውስጡ ላይ ለይቶ ለማውጣት የፀሐፊውን ሀሳብ ይመረምራል፡፡ እንዲሁም ንባብ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ስያሜዎች ቢሰጡትም የስያሜዎቹ ትኩረት ግን አንድን ፅሁፍ አንብቦ ከመረዳት፣መረጃን ከመቀበልና በንግግር የሚቀርብ መልዕክትን በፅሁፍ ሰፍሮ ከሚያገኙት አንፃር የሚያጠነጥኑ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም የምንረዳው ምሁራን ለንባብ የሚሰጧቸው የተለያዩ ብያኔዎች ቢኖሩም ትኩረታቸው አንድን ፅሁፍ አንብበው የፅሁፉን መልዕክት መረዳት ላይ መሆኑ ነው፡፡ Williams(1990:2) እንደገለፁትው “ንባብ ቀለል ባለ ፍቺው አንድን ፅሁፍ ተመልክቶ በፅሁፍ የቀረበውን ሀሳብ መረዳት መቻል ነው” ይሉታል፡፡ በዚህ የንባብ ፍቺ ላይ Williams ትኩረት ያደረጉባቸው ሁለት አበይት ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው “ፅሁፉን መመልከት” ሲሆን ይህም አንባቢ በቀረበለት ፅሁፍ ላይ የሚያደርገውን እይታ የሚመለከት ነው፡፡ጥሩ አንባቢ በሚያነበው ፅሁፍ ውስጥ ያሉ ፊደላት በሥርዓት ተቀናጅተው የሚመሰርቷቸውን ቃላት በቡድን በአንድ ላይ አያይዞ በመመልከት የሚያነብ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛው ከንባብ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ዐቢይ ጉዳይ የፅሁፉን ሃሳብ መረዳት ነው፡፡ይህም አንባቢ በፅሁፍ ውስጥ የቀረበውን መልዕክት ወይም ሀሳብ በተቻለ መጠን ለማወቅ የሚያደርገውን ጥረት የሚያመለክት ነው፡፡

## 2.2 የማንበብ ተነሳሽነት

የማንበብ ተነሳሽነት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በተለያዩ አውዶች ውሰጥ የተለየ ትርጉም አለው፡፡የማንበብ ተነሳሽነት ማንኛውንም ስራ ለማበርታት ተደጋግሞ የሚቀርብና ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡Brown (1994) እንዳብራሩት የማንበብ ተነሳሽነት የሚለው ሃሳብ ማንኛውን የስኬታማነት መገለጫ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ተነሳሽነት አንድ ሰው አንድን ተግባር ለመፈፀም የሚኖረው ውስጣዊና ውጫዊ ግፊት ሲሆን ይህ ውስጣዊና ውጫዊ ግፊት በቋንቋ ትምህርት ረገድ ግለሰባዊ ልዩነት ከሚፈጥሩ መንስኤ ውስጥ ይካተታል፡፡ ተማሪዎች ወደ ክፍል ይዘውት የሚመጡት ተነሳሽነት ለውጤታቸው መሻሻል አይነተኛ ሚና እንዳለው ይገልፃሉ(Feng & Yung2013):: Guthrie & Wigfield (2000) የማንበብ ተነሳሽነትን

በማብራራት እንዳስቀመጡት የንባብ ተነሳሽነት ማለት እያንዳንዱ ዓላማ፣ጥቅም እና እምነት ከርዕሱ፣ ከሂደቱና በንባብ ውጤት መካከል የሚደረግ የእርስ በርስ ግንኙነት ነው። ተነሳሽነት ያለው አንባቢ የራሱ የሆነ ዓላማ ፣የመረዳት ፍላጎት፣ ውጤታማነትና ባለቤትነት አለው። ውስጣዊ ተነሳሽነት (Intrisic motivation) ወይም ውጫዊ ተነሳሽነት (Extrisic motivation) አንባቢን ለንባብና ለመረዳት የሚያነሳሱ ምክንያቶች ናቸው። ውስጣዊ መነሳሳት የሚመጣው ከራሱ ከአንባቢው ነው።ውስጣዊ የአንባቢ ተነሳሽነት ለመማርና ለማወቅ የራሱ የሆነ ዓላማ ሲኖረው በራስ ተነሳሽነት ማንበብ፣የማወቅ ፍላጎትን ለማሟላት ማንበብ ወይም ፈታኝ የሆኑ ሀሳቦችን ለመጋፈጥ ማንበብን ይመለከታል (Alexander & Jetson 2000):: በዚህ ላይ የራስ ውሳኔ አንባቢያን በጥልቀት ለማንበብ፣ሀላፊነትን ለመውሰድ ፣የመማር እድልን መፍጠርና ፈታኝ የሆኑ ፅንሰ ሃሳብን መጋፈጥ ናቸው።

ውጫዊ የንብብ ተነሳሽነት የሚያጠቃልለው እውቅና መስጠትን ፣ ውድድርን ጫና ማስወገድ/አንባቢው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለንባብ የሚጠፋውን ጊዜና ጉልበት መቀነስ/ ናቸው (Guthrie 1996)። በውጫዊ ምክንያቶች የተነሳሳ አንባቢ የሚያነበው እውቅናንና ሽልማቶችን ለማግኘት እንጂ ከንባቡ እውቀትን አገኛለው ብሎ አይደለም ጠንካራዎቹ የውጫዊ የንባብ ተነሳሽነት ምክንያቶች የተማሪዎች ውጤት አድናቆት፣ማበረታቻና አውቅና ማግኛ ናቸው (Guthrie & Wigfield 2000)። የንባብ ተነሳሽነት ሂደታዊና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየዳበረ የሚመጣ ባህሪ ነው። የንባብ ተነሳሽነት ለተማሪዎች የንባብ ውጤታማነትና የትምህርት ቤት ስኬት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በተጨማሪም Guthrie & Wigfield በመረጃ በማስደገፍ እንዳረጋገጡት የንባብ ተነሳሽነት የልጆችን የንብብ መጠንና የንባብ ግንዛቤ ለመተንበይ ይረዳል።

Guthrie & Wigfield Metsata Cox (1999) ምሁራን ግኝት ከሆኑ የንባብ ተነሳሽነት ለንባብ ግንዛቤ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያሳያል። በተጨማሪም ምሁራኖቹ እንዳስቀመጡት የንባብ ተነሳሽነትን ሊጨምሩ የሚችሉ የመማሪያ ስልቶች የሚከተሉት ናቸው።

- የንባቡን ዓላማ መስቀመጥ
- ተማሪዎች በራስ የመስራት ችሎታ እንዲኖራቸው መርዳት
- ፍላጎትን የሚጭሩ ፅሁፎችን ማቅረብ
- ከንባቡ ጋር የተያያዙ ማህበራዊ መሰተጋብር ማድረግ
- በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ

- ፍላጎትን ለማነሳሳት አካላዊ እንቅስቃሴ መጠቀም
- በክፍል ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት ላይ ማተኮር (ለንባብ ተነሳሽነት ላላቸው ተማሪዎች እውቅና መስጠት፣ ማበረታታት፣ ስህተትን ማረም፣ንባቡ ላይ ውይይት እንዲያደረጉ ማድረግ፣ በግል የንባብ ጥረት እንዲያደርጉ መጋበዝ)።

## 2.3 አንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት መሰብሰብ መቻል ማለት ነው። በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እየለየ በመተው የሚፈልገውን መረጃ ብቻ ሊመርጥ ይችላል ። ይህም አንድ መሰረታዊ አሀድ ከመርዳቱም በተጨማሪ የአሀዱን ዝርዝር በብቃት የሚገነዘብበት ሁኔታ የሚጠቃለለው እዚሁ ውስጥ ነው በማለት አለም (1991) ይገልጻሉ።

Nuttall (1996) እንደገለጹት ደግሞ አንብቦ መረዳት ማለት ለንባብ የቀረበው ጽሁፍ እና የአንባቢው አእምሯዊ እውቀት እንዲሁም ስነልቦናዊ ችሎታ በሂደት በማገናኘት ለተጻፈው ጹሁፍ ትረጉም መስጠት ነው። ንባብ በባህሪው ውስብስብ የሆነ አእምሯዊ ተግባር በመሆኑ ትኩረትን የሚጠይቅና ጸሀፊው በጻፈው ሀሳብ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ከራስ ገጠመኝ ጋር በማገናዘብ ምላሽ መስጠትን የሚፈልግ ክሂል ነው።

በተጨማሪም Sheng (2000) የተባሉ ምሁር አንብቦ የመረዳት ተግባርን በሁለት ከፍለው ሲያብራሩ የመጀመሪያው ተግባር በምንባቡ ውስጥ ግለጽ ሆነው የተቀመጡ ወይም የቀረቡ ሀሳቦችን መገንዘብ ሁነቶችን (Evenets) ፣ድረጊቶችን ፣ ክስተቶችን ወዘተ የአቀራረብ ቅደም ተከተል ማስታወስን እንዲሁም በጽሁፍ ውስጥ የተቀመጡ ልዩነቶችና ተመሳሳይ ባህሪያቶችን መለየትን የምክንያትና ውጤት ቁርኘትን ማስታወስን ወዘተ ገልጸዋል። ሁለተኛው አንብቦ የመረዳት ተግባርን ሲገልጹ ደግሞ ተማሪዎች ያላቸው እውቀትና ግምት በመጠቀም በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ ያልተቀመጡ ሃሳቦችን አንብበው የሚረዱበት ሁኔታ ነው ።በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ የተገለጸውን አንብቦ የመረዳት ተግባርን ለመከውን በንባቡ ወቅት አንባቢው የሚፈጽማቸው ክንውኖችም የንባቡን ሀሳብ መለየት ፣ፍሬ ሀሳቡን መለየት ፣ደጋፊ ሀሳቦችን መለየት ፣ከምክንያትና ውጤት ትስስር ምክንያት ሊፈጥር የሚችለውን መተንበይ ፣በንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን ፍንጭ በመጠቀም የገጸባህሪያትን ባህሪ መረዳትና ጻሀፊው የተጠቀመበትን የቋንቋ ፍቺ መለየትን ያጠቃልላል (Sheng 2000)::

ሌላው Smith (1985:124) አንብቦ መረዳት አንባቢ ይዞት ለሚነሳው ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነው፡፡ የሚነበብን ፅሁፍ አስመልክቶ ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ባህሪ ነው፡፡ አንባቢ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢውና በፀሐፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያሳያል፡፡ በፅሁፉና በአንባቢው መካከል ተግባቦት አለ ማለት የሚቻለውም መረዳት ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም አንብቦ መረዳትንና ተግባቦትን መለያየት አይቻልም ማለት ነው፡፡ ባጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ነው ልንለው እንችላለን፡፡

ተስፋዬ (1986፡9) "አንብቦ መረዳት ማለት ያነበቡትን ምንባብ እንዲሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ሳይሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ስለአነበቡት ምንባብ መጠየቅን፣የምንባቡን አጠቃላይ እና ዝርዝር ሀሳብ መመርመርን፣ማመዛዘን እና ቀደም ሲል ካለ እውቀት ጋር ማመሳከር የሚጠይቅ ተግባር ነው" ሲሉ ከላይ የምሁራኑን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡ ስለዚህም እንብቦ መረዳት የፀሐፊውን ሀሳብ እንዳለ መውሰድ ወይም አለመውሰድ ሳይሆን የምንባቡን አጠቃላይ እና ዝርዝር ሀሳብ የመገንዘብ እና የመለየት ሂደት መሆኑን ነው፡፡እስካሁን ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳ እንደሚቻለው አንብቦ መረዳት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ከመገንዘብ ባሻገር ጠቃሚና አዳዲስ መረጃዎችን ለቅሞ ለማውጣት የሚያስችል ሂደትና የምንፈልገውን ደግሞ የምንተውበትን ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡

## 2.4. የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

አንድን ፅሁፍ አንብቦ መልዕክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣በማንበብ አጠቃላይ እውቀትን ለመገብየት፣ከተለያዩ የንባብ ባህሪያት ጋር ለመተዋወቅና ሂሳዊ የንባብ ችሎታን ለማጎልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ ነው (Williams (1990፡19 እና Grant 1990:60):: ንባብ አዲስ መረጃን ለማግኘትም ሆነ ክሂሎችን ለማዳበር መሠረት ሊሆን እንደሚችል Williams(1984) የሚከተሉትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎች በማዳመጥ እና በመናገር ያላገኙትን ነገር በንባብ አግኝተው ቋንቋውን ይበልጥ እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡

- አንድን ምንባብ አንብበው ምን ማስተላለፍ እንደተፈለገ በቀላሉ መግለፅ ያስችላቸዋል፡፡
- ከቋንቋ ትምህርቱ በተጨማሪ ተማሪዎች አካባቢያቸውን ሀገራቸውን እንዲሁም በአለም ዙሪያ ያሉ ነገሮችን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል፡፡

- ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው በሚያደርጉት ውይይት በተጓዳኝ የንግግርን ክሂልን ለማስተማር ያስችላል፡፡
- ተማሪዎች የምንባቡን ሐሳብ ተረድተው የሚፈልጉትን መረጃ ከምንባቡ ውስጥ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለመማር ይረዳቸዋል፡፡
- ከንባብ ክሂል ባሻገር የፅህፈት፣የቃላት፣ የሰዋስው፣ወዘተ እውቀታቸውን ለማሳደግ ይረዳል፡፡
- ተማሪዎች ከተለያዩ ገጠመኞች ጋር እንዲተዋወቁ እና እንዲዝናኑ ያስችላል፡፡
- ተማሪዎች መሰረታዊ የሆነ የአንብቦ መረዳት ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

የንባብ ትምህርት የራሱ ግብና ስልት ያለው ሲሆን ራሳቸውን ችለው አቀላጥፈው ማንበብና መረዳት የሚችሉ ተማሪዎችን ለማፍራትም በጣም አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው (Ur 1996:15)፡: ንባብ የአንድን ህብረተሰብ ዳራዊ ሁኔታ ወይም መሠረት፣የሌሎችን ዓለማት ሰዎች የአኗኗር ዘዴና ባህል ለማወቅ ይረዳል፡፡ ንባብ ለትምህርት ብቻ ሳይሆን በህይወታችን ለምንፈፅመው ማንኛውም ተግባር መረጃ በመስጠት ጠቋሚ ሚና ይጫወታል፡፡

## 2.5 የንባብ ትምህርት አላማ

ማረው (1998) እንደሚያስረዱት በተማሪዎች ዘንድ አንብቦ መረዳት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለማስወገድ የሚነበበው ጽሁፍ ምን አይነት ጽሁፍ ነው? የማነበው ለምን አላማ ነው ? የማነበው በምን አይነት ስልት ነው የሚሉትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህን በመረዳት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን በላቀ ደረጃ ማሳደግ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የተጻፉ ጽሁፎችን ለተለያዩ አላማዎች ለማንበብ ሲነሱ የሚያነቡበት የንባብ አላማ እንደ ፍላጎታቸው ይለያያል የሚያስገኘውም ጠቀሜታ እንደሚያነቡት ዋና አላማ የተለያየ ቢሆንም ጠቀለል ባለ መልኩ ግን የማንበብ አላማ ምንባብ ለመዝናናትና ምንባብ እውቀት ለማግኘት በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡

## 2.6 የንባብ ስልቶች

የንባብ ስልቶች እንደ ፅሁፍ አይነት ወይም እንደ አንባቢው ዓላማ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ Williams (1984) እንደገለፁትም የተለያዩ ፅሁፎችን ለተለያየ ዓላማ ለማንበብ የሚያስችሉ

ስልቶች ጥልቅ ንባብ፣የምልከታ ንባብ፣የአሰሳ ንባብ እና ሰፊ ንባብ በመባል እንደሚታወቁ ይገልፃሉ።እ ነሱም በዝርዝር ቀርበዋል።

ጥልቅ ንባብ:- ይህ የንባብ ሂደት ከፍተኛ ትኩረት እና ጥንቃቄን የሚጠይቅ የንባብ ስልት ነው። ምክንያቱም በፅሁፍ የሰፈረውን መልዕክት ለመረዳት እያንዳንዱን ቃል፣ሐረግ ወይም ዐ.ነገር በጥልቀት በመመርመር ሀሳቡን በተገቢ መንገድ መረዳትን ይጠይቃልና ነው። ይህ የንባብ ስልት አመራማሪ የሆኑትን ጥልቅ ፅንሰ ሃሳቦችን የያዙ ፅሁፎችን በአንድ ጉዳይ ላይ የተፃፈ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማግኘት የሚነበብበት ነው፤ የተወሰኑ ሀሳቦችን በዝርዝር ለመረዳት ከፍጥነት ይልቅ ጥልቀትን መሠረት በማድረግ በመደበኛው የንባብ ፍጥነት ይከናወናል (Williams 1984፤ Grellet 1981) ።

የምልከታ ንባብ፡- ይህ የንባብ ስልት እንድን ፅሁፍ ከዳር እስከ ዳር ሙሉ በሙሉ ማንበብን አይጠይቅም። በአንድ ጊዜ ብዙ ቃላትን በአይናችን በመቃኘት ከአሀዱ ውስጥ በአጠቃላይ መረጃን ማግኘት ነው። ስለፅሁፍ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘትወይም ለመጨበጥ በፍጥነት የሚከናወን የንባብ ስልት ነው( Williams 1984፤ Grellet 1981)። በዚህ የንባብ ሂደት ትኩረት የሚደረገው በፅሁፍ ውስጥ የየአንቀፁን መንደርደሪያ ዐርፍተ ነገር ለይቶ በማውጣት የፅሁፉን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ነው።

የአሰሳ ንባብ፡- ይህ የንባብ ስልት በፍጥነት የሚካሄድ ሲሆን ከፅሁፍ ውስጥ ይጠቅመናል ብለው የሚያስቡትን አንድ አስፈላጊ መረጃ ነጥሎ ለማውጣት እና ለይቶ ለመረዳት የሚከናወን ሂደት ነው( Williams 1984፤ Grellet 1981)።በአሰሳ ንባብ የሚፈለገውን አጠቃላይ ወይም ዝርዝር ሀሳብ ሳይሆን የተወሰነ መረጃ ከምንባቡ ፈልጎ ለማግኘት፣የቃላት ድግግሞሽን ለማየት፣ስሞችን፣ቀኖችን፣ዓመተ ምህረቶችን እና የተለያዩ መረጃዎችን በፍጥነት አይንን በምንባቡ ላይ በማንቀሳቀስ ለይቶ ለማውጣት የሚያገለግል ስልት ነው።

ሰፊ ንባብ:- ይህ የንባብ አይነት ከጥልቅ ንባብ፣ከምልከታ ንባብ እና ከአሰሳ ንባብ የሚለየው ሰፊ ጊዜ የሚወስድ መሆኑ ነው። ይህ የንባብ ስልት እንደ ረጅም እና አጭር ልቦለድ ያሉ ሰፊ ጊዜን የሚጠይቁና የተለያዩ ይዘቶችን፣ቅርፆችን ያካተቱ ፅሁፎችን የያዙ ምንባቦች የሚነበቡበት ሂደት ነው። የዚህ የንባብ ስልት ዋነኛ ዓላማ ማዝናናት ሲሆን በተጓዳኝም እውቀት ሊያስጨብጥ ይችላል። አሀዱ ሰፊ እንደመሆኑ መጠን አጠቃላይ ግንዛቤን ለማግኘት ይከናውናል (Williams 1984፤ Grellet 1981) ።

## 2.7 የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች

ልማዳዊ (Traditional )በምንለው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ ሂደት ላይ ተማሪዎች እንዲያነቡ ይደረግና መምህሩ ሲያነቡ እንዲያዳምጡ ይደረግ ነበር። አስፈላጊም ሲሆን ተማሪዎቹ በቀጥታ እንዲያነቡ በማድረግና ሲጨረሱም ተከታታይ እና በርካታ ጥያቄዎችን ማሰራት ነበር። ይሁን እንጂ ይህ የንባብ ትምህረት አካሄድ ተማሪዎችን ውጤታማ የማንበብ ችሎታ እንዲኖራቸው አያደርግም።Mera Rivas(1999)እንደሚያስረዱት ይልቁንም ክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ቅድመ ንባብ ፣የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ በሚሉት ሶስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ መቅረብ ይኖርበታል።በመሆኑም እያንዳንዳቸውን በቅደም ተከተል እንመልከት።

### ሀ. ቅደመ ንባብ (pre- reading)

ተማሪዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የሚተገበር ሲሆን በሚነበበው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚዳሰስበትና የማነቃቃት ስራ የሚሰራበት ደረጃ ነው።ሆኖም ተማሪዎች ከቀደመ እውቀታቸው በመነሳት ስለምንባቡ አንዳንድ ጉዳዮችን በማንሳት ውይይት ማድረግ ይኖረባቸዋል።ሆኖም በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥም ዋናዋናዎቹ ርእሱን ማስተዋወቅ ተጠቃሽ ናቸው።

### ለ. የንባብ ጊዜ (While —reading)

ይህ የንባብ አቀራረብ ደረጃ ምንባቡ በጥልቀት የሚነበብበት ደረጃ ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎቹ የጽሁፉን ይዘት እና መዋቀር እንዲሁም የጸሐፊውን ወነኛ ዓላማ እንዲረዱት ማስቻል ነው።ሆኖም ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ያስፈልጋል ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግም የተለያ ጥያቄዎችን መጠቀም ይቻላል። ከነዚህም ውስጥ Celce Muria(1991) እንደገለጹት ጥያቄዎቹ ሶስት አንብቦ የመረዳት ደረጃዎችን ማካተት ይኖርባቸዋል። እነሱም በግልጽ የቀረቡ መረጃዎችን የሚመለከቱ ውስጣዊ መልዕክታቸውን በመመርመር የሚቀርቡና አዲሱን መረጃ ከቀደመ እውቀት ጋር በማገናዘብ የሚመለሱ ጥያቄዎች ሲሆኑ ይገባል በማለት ያብራራሉ።

### ሐ. ድህረ ንባብ (Post — reading)

ይህ የንባብ ደረጃ ተማሪዎች ከምንባቡ ያገኙትን መረጃ በመንገዘብ ወደ እራሳቸው ህይወት የሚተረጉሙበት እና ስለምንባቡ ያላቸውን አጠቃላይ የግንዛቤ ሃሳብ እና አስታየታቸውን

የሚያንጸባረቁበት ደረጃ ነው፡፡በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ የምንባቡን ሀሳብ በራስ ግንዛቤ በመግለጽ ከራስ እውቀት ፣አመለካከትና ፍላጎት ጋር ማዛመድ የመሳሰሉት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከነዚህ ሶስት ደረጃዎች እርስበርስ የተደጋገፉና አንዱ ሌላውን በመደገፍ የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት የሚስችሉ ስልቶች ናቸው፡፡ ሆኖም አንዳንድ መምህራን ቀድመ ንባብን በማስቀረት ተማሪዎች በቀጥታ ወደሚነበበው ዋና ዕርሰ ጉዳይ ገብተው እንዲያነቡ የሚያደርጉበት ወይም ድህረ ንባብን አስፈላጊ አይደለም በማለት የሚተዉበት አጋጣሚ አለ፡፡ይህም በክፍል ውስጥ ትግበራ የሚታይ ችግር ነው ፡፡ እንዲህ አይነቱ ትግበራ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ሶስቱም የንባብ ደረጃዎች ቢተገበሩ ደግሞ ሁለት ዋናዋና ጠቀሜታዎች እንዳሉት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ አንደኛው ዋነኛ ጠቀሜታ ተማሪዎቹ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲሳተፉ እንዲነሳሱና የበለጠ መሻሻል እንዲያሳዩ ያስችላል፡፡ሁለተኛው ወነኛ ጠቀሜታ ደግሞ የንባብ ክሂል ከሌሎቹ ጋር አዋህዶ ለማስተማር ያስችላል፡፡ በመሆኑም ደረጃዎችን ተግባራዊ ማድረጉ የተሻለ የንባብ ትምህርትን ለማቅረብ እንደሚረዳ (Williams 1984)ይገልጻሉ ፡፡

## 2.8 አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን

በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ ምሁራን (Madson 1983, Weir 1990, Davey 1987, Stavans 1993) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናትም አንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች ለተማሪዎች ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም ስለ አንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ማነሳት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 2.8.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና

የችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የፈተናዎቹ አስተማማኝነት (Reliability) እና ትክክለኛነት (Validity) ታሳቢ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Heaton 1991፣ Bachman 1990 ፣ Hughes 1995:: ትክክለኛነት ለመፈተን የተፈለገውን ችሎታ ወይም ክሂል በትክክል መለካት መቻሉን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን፤አስተማማኝነት ደግሞ አንድ ፈተና ተደጋግሞ ቢሰጥ

የሚያስገኘው ውጤት ያለውን ተቀራራቢነት የሚያመለክትነው(Bachman 1990፣Hughes 1995 )።

ችሎታ መመዘኛ የሚዘጋጅ ፈተና በትክክል የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል ሲሆኑ በባለሙያዋች ሊታይና አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል።እንዲሁም አንድ ፈተና በስፋት ከመሰጠቱ በፊት የሙከራ ፈተና (Pilot test) በመስጠት አስተማማኝነቱን መለካት አስፈላጊ ይሆናል (Weir 1990 ፣ Heaton 1991 ::

የአንብብ መረዳት ፈተና ሲዘጋጅ የተፈታኞች የንባብ ፊላጎት ለመጠበቅና እኩል እድል ለመስጠት ቢያንስ ሁለት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ምንባቦች ተመርጠው ጥያቄዎቹ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። የምንባቦቹ የተነባቢነትሰ ደረጃ  በፈተናው ውጤት ላይ ተጽዕኖ ስለሚኖረው በጥንቃቄ መመረጥ ተገቢ ይሆናል (Madson 1983 :89) ።

በ Madson( 1983 :90) አከፋፈል መሰረት የምንባቦቹ ርዝመት እደተፈታኞቹ የክፍል ደረጃ ሊለያይ የሚችል ሲሆን ለዝቅተኛ ወይም ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ከ 100 እስከ 200 ቃላት ፣ለመካከለኛ ደረጃ ከ 150 እስከ 300 ቃላት የያዙ ምንባቦች ሊመረጡ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ። Heaton (1991: 112) ደግሞ ለስቅተኛ ክፍል ከ50 እስከ 100 ቃላት፣ለመካከለኛ ደረጃ ከ 200 እስከ 300 ቃላት እና ለከፍተኛ ደረጃ ከ400 እስከ 600 ቃላት ያላቸው ምንባቦች ሊመረጡ እንደሚችሉ ያመለክታሉ።ለአንብቦ መረዳት ፈተና የሚያስፈልገውን ጊዜ በሙከራው ፈተናው ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ሲሆን 80 በመቶ ጥጥቄዎች እስኪመለሱ ድረስ በቂ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል(Madson 1983 :90) ::

ከዚህ በተጨማሪ የተፈታኞችን አንብቦ መረዳት ችሎታ በመፈተን መረጃ ለመሰብሰብ የሚዘጋጁ ፈተናዎች በግምት ወይም በቀደመ እውቀት እና ጥያቄዎችን ከምንባቡ ጋር ቃልበቃል በማመሳሰል የማይመለሱ ፣ከቀላል ወደ ከባድ ደረጃ በደረጃ የሚሸጋገሩ ፣አጭርና ግልጽ እንዲሁም ድርብ አሉታ አረፍተ ነገሮች የሌሉባቸው መሆን ይገባቸዋል (Hughes 1995: 119 -135፣ Madson 1983: 93፣Heaton 1991: 121)

## 2.9 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለመመዘን የተለያዩ ፈተናዎች ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ተፈታኝ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው ወይም የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው

ከሚጠበቀው በላይ ወይም በታች ነው ለማለት የሚቻለው የተፈታኙ ውጤት ከምን ደረጃ ደረሶ ሲገኝ ነው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ Hughes(1995፡119)እንደ ሚገልጹት በመሰረቱ አንድ ጹሁፍ የያዘውን ሀሳብ ወይም መልዕክት ተፈታኞች ሙሉ በሙሉ ተረድተውታል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል ፡፡ ነገር ግን የሰው አእምሮ በጽሁፍ የቀረቡ ሃሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የሚገነዘብ በመሆኑ ይህ ሁል ጊዜም ይሳካል ማለት እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የአንብቦ መረዳት ተፈታኞች ከ80 በመቶ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የቀረበውን ጽሁፍ ተረድተውታል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ Nuttall(1987:37)ደግሞ በአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈታኞች 70 በመቶ እና ከዚያም በላይ ውጤት ካስመዘገቡ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳለቸው ያስገነዝባል፡፡

Narayanswamy,(1975:144-147) የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ተገናዝቦ መተየት የሚገባው ሲሆን ተፈታኞች በማንኛውም ጊዜ በሚያነቡበት አማካይ የንባብ ፍጥነት የቀረበላቸውን ጽሁፍ አንብቦ 70 ከመቶ ካገኙ ጥሩ አንብቦ መረዳት ችሎተን አላቸው ማለት ይቻላል ይላሉ፡፡ በመቀጠለም የተፈታኞችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዘርዘር ባለ መልኩ ከፋፍለው በማመልከት ከ 10 ከታረመ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና 9 እና 10 ያገኘ ተፈታኝ ከፍተኛ ችሎታ ያለው፣ ከ7 እስከ 8 ያገኘ ተፈታኝ በቂ ችሎታ ያለው ሲሆን በአንፃሩ ከ 5 እስከ 6 ውጤት ያገኘ ተፈታኝ ዝቅተኛ እና ከ5 በታች ያስመዘገበ ተፈታኝ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተደርጎ ተወስዷል፡፡ አንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ማግኘት ያለበትን ውጤት በተመለከተ Nuttall(2000)፣ Narayanaswarmy (1975) በተመሳሳይ ውጤት ይስማማሉ፡፡

ከዚህ በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በሰነዘሯቸው ሀሳቦች መሠረት ተማሪዎች በሚሰጣቸው አንብቦ የመረዳት ፈተና ከሚያገኑት ውጤት በመነሳት የሚያገኙበትን ደረጃ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ**

| ተ.ቁ | ውጤት | | ደረጃ |
|---|---|---|---|
| | ከ10 | ከ100 | |
| 1 | 9 -10 | 90 - 100 | ከፍተኛ |
| 2 | 7 — 8 | 70 — 80 | መካከለኛ/በቂ/ |
| 3 | 5 — 6 | 50 — 60 | ዝቅተኛ |
| 4 | ከ 5 በታች | ከ 50 በታች | በጣም ዝቅተኛ |

ምንጭ፡- Hughes (1995) ፣ Nuttall (1997) ፣ Narayanaswarmy (1975) ን መሰረት በማድረግ እና ሰንጠረዥ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## 2.10. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ጥናታዊ ርዕስ ከዚህ ቀደም የተጠኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው የተወሰኑ ጥናቶችን ለመዳሰስ ጥረት አድርጋለች፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን በነጌሌ ቦረና ከተማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ ላይ በመሆኑ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ማግኘት ባይቻልም በተዘዋዋሪ ተቀራራቢ የሆኑ ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡

በዚህ መሠረት አጥኚዋ ለጥናቷ በመረጠችው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ አራት ያህል ቀደምት ጥናቶችን የተመለከተች ሲሆን እነዚህም ጥናቶች ሁሉም በአንደኛ ደረጃ 2ኛሳይክል ትምህርት ቤት በሚማሩ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው አስቴር (2010) በባህር ዳር ክፍለ ከተማ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድረሻ፤አምስተኛና በሰባተኛ ክፍል

ተማሪዎች ተተኳሪነት ጥናታቸውን አከናውነዋል፡፡  የአስቴር ጥናት አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡አጥኚዋ ለጥናቷ የመረጠችው ቦታ  ባህር ዳራ ፣ ለመረጃ መሰብሰቢያነትም የጽሁፍ መጠየቅ ፣አንብቦ መረዳት ፈተና ና የቡድን ውይይት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡  ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤትም ተማሪዎች ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተገናኘ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን እና የማንበብ ተነሳሽነታቸውን የሚያዳብርላቸው የቤተሰብ ትምህርት ደረጃና የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ወይም በከፍተኛ ደረጃ ይተነብያል ሲሉ ገልጸዋል ፡፡ የአስቴር ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ማተኮሩ፣በመረጃ መሰብሰቢያ ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣አንብቦ የመረዳት ፈተና ሲሆን  ልዩነታቸውን ስናይ የአስቴር ጥናት ከቦታ አንፃር ባህር ዳር  ከጊዜ አንፃር(2010) የክፍል ደረጃቸው የ5እና የ7ኛ  ክፍል ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አኳያ ሶስት የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን የተመለከተ ሲሆን እንደዚሁም የመረጃ መሰብሰቢያና የአጠናን  ዘዴው ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

ሁለተኛው እንድሪስ  (2009) በቴክስት ውቅር ብልሀቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ በስድስተኛ ክፍል ተተኳሪነትበሚል ፈተሸዋል፡፡የእንድሪስ ጥናት አላማ በቴክስት ውቅር ብልሃቶች ማንበብን መማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት፣ ግለብቃት እምነት ትኩረትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተጽዕኖ መፈተሸ ነው፡፡አጥኚው ለጥናቱ የመረጠው ቦታ አዲስ አበባ ፣መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የአንብቦ መረዳትና የማንበብ ትኩረት መለኪያ ፈተናዎች፣የማንበብ ግለበቃት እምነትና የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቆች ተጠቅሟል፡፡ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማንበብ ክሂል የማስተማር ዘዴዎቻቸው ውስጥ ተማሪዎቹ እንደሚያነቧቸው ቴክስቶች ባህሪያት የሀሳብ አደረጃጀቶችን እየለዩ ፣ሀሳቦችን እርስበርስ ያሏቸውን ቅድምተከተላዊ ግንኙነት ፣የምክኒያትና የውጤት ትስስር፣የችግርና መፍት ሄቁርኝት፣መሳስሎና ልዩነት መረዳት የሚያስችሉ የቴክስት ውቅር ብልሃቶችን በመጠቀም ቢያስተምሩ የተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ፣ማንበብ ግለብቃት እምነት የማንበብ ተነሳሽነትና የማንበብ ትኩረት የሚሻሻልበት ሁኔታ ይፈጥራል ሲል ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ሁለቱ ጥናቶች የሚያመሳስላቸው በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ላይ መሰራታቸው ከደረጃቸው አንጻር አንደኛ ደረጃ ላይ ማተኮራቸው እንዲሁም

በተወሰኑ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎቹ ሲመሳሰሉ ልዩነታቸው የእንድሪስ ጥናት ከቦታ አንጻር አዲስ አበባ የክፍል ደረጃቸው ስድስተኛ ክፍልን ፣ከጊዜ አንጻር በ2009 መሆኑ እንዲሁም ጥናቱ በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብና መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ የፈተሸ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሸ በመሆኑ ልይነቶች ታይቷል፡፡

ሶስተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረበው የዘውዱ(2008) ሚና ለዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ፈትሿል፡፡ የዘውዱ ጥናት ዓላማ ሚና ለዋጭ ዘዴ የአማረኛ አፈ ፈት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም ጥናቱ ፍትነታዊ መሰል (Quasi-expermentale) ስልትን የተከተለ ሲሆን የፅሁፍ መጠይቅ፣የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ፈተናን ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በየዓይነታቸው ከተደራጀው በኃላ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታስቲክ (የነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስትና ዳግም ልኬት ቲ-ቴስት) በመጠቀም መተንተኑ ተገልጿል፡፡ ከዚህም በመነሳት ሚና ለዋጭ ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ከተለመደው የማንበብ ማስተማሪያ ዘዴ የበለጠ አስተዋፅኦ አለው ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

ይህም ሚና ለዋጭ ዘዴ ማንበብን በማስተማር ሂደት አእምሮአዊ ብልሀቶቹ ያላቸውን የክብደት ደረጃ ከግምት ባስገባ መንገድ ተግባር ላይ ቢውሉ መልካም ነው የሚል አንድምታን አሳይቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አንብቦ የመረዳት ችሎታን በመፈተሸ፣አፈ ፈት ተማሪዎች መሆናቸውና የክፍል ደረጃቸው (7ኛ ክፍል) መሰራታቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የዘውዱ ሚና ለዋጭ ዘዴ ትኩረት በማድረግ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሳደግ የሚኖውን ሚና ሲፈትሽ፣ ከቦታ፣ከጊዜየመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ልዩነቶች ፈጥሯል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር አንብቦ መረዳት ችሎታን በመፈተሽ አማረኛ አፍ ፈት ተማሪዎች መሆናቸው እንዲሁም የክፍል ደረጃቸው 7ኛ ላይ በማተኮር መስራታቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ልዩነታቸው ደግሞ የዘውዱ ጥናት ሚናለዋጭ ዘዴን ትኩረት በማድረግ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሳደግ የሚኖረውን ሚና ሲፈትሽ፣ከቦታ አንፃር በአማራ

ክልል መካሄዱ ከጊዜው አንፃር (በ2008) መከናወኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የክፍል ውስጥ ምልከታ ማካሄዱ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት ፈጥሯል፡፡

አራተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረበው ሌላኛው ጥናት ሒሩት/2008) በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሂርና ከተማ በተመረጠ የመንግስት ትምህርት ቤት በአማረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈትሸዋል፡፡ የሒሩት ጥናት ዓላማ በአማረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ ነው፡፡ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ለመረጃ መሰብሰቢያነትም አንብቦ የመረዳት ፈተና፣የፅሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በአማረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሂርና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገልፃለች፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናትጋር የሚያመሳስለው አንብቦ መረዳት ላይ መስራታቸው፣አፍ ፈት ተማሪ ላይ ማተኮራቸው፣ከደረጃቸው አንፃር 1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ መሆኑ እንዲሁም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ሆኖም ግን፤ ከቦታ አንፃር በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሂርና ከተማ፣ከጊዜ አንፃር በ2008 የተካሄደ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ልዩነቶች ታይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ቢመሳሰሉም የሁሉም ጥናት ትኩረት ግን የተለያየ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ጥናቶች አንድ የሚያደርጋቸው የፅሁፍ መጠይቅና አንብቦ የመረዳት ፈተናዎችን በመረጃ ምንጭነት መጠቀማቸው ነው

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና  የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የሚገኝበትን ደረጃ ለመገምገም መሆኑ ቀደም ሲል በጥናቱ ደራና ዓላማ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በጥናቱ የተካተቱት የናሙና አመራረጥና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ቀደም ሲል በጥናቱ ወሰን ላይ እንደተገለፀው በዚህ ጥናት አንድ የ1ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ተተኳሪ ሆኗል፡፡ይህን ትምህርት ቤት ለመምረጥ ከወረዳው ትምህርት ቤቶች ፅህፈት ቤት በተገኘው መረጃ መሠረት በመጀመሪያ በከተማው ከሚገኙ “8” 1ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የሚማሩበትና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት እንዲለይ ተደርጓል፡፡

ይህም ሾላ 1ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ብቻ በመሆኑ በአላማ ተኮር ዘዴ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ተወስዷል፡፡ ምክንያቱም ያለው (2009፡136) እንደገለጹት በዚህ ንሞና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ አላማ አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብንመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡን ይችላሉ? የትኞቹ የጥናት አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ሳገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ነገሮችን ይመርጣል፡፡በመሆኑም በወረዳውም ሆነ በነጌሌ ቦረና ከተማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበት ከላይ የተጠቀሰው ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡

### 3.1.2 የተማሪዎች አመራረጥ

ለጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበትን ትምህርት ቤት ተለይቶ ከታወቀ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር ተጠኝ ተማሪዎች መምረጥ ነው፡፡ በዚሁ ናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ

በ2015 ዓ.ም በመደበኛነት በ7ኛ ክፍል ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ና የሚማሩበትን ምድብ መሠረት በማድረግ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ(comprehensive sampling) ተወስደው በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነው ያለው (2009) እንደገለፁት እና ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ተመራማሪው ያገኛቸውን ሁሉንም የጥናቱን አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድርጎ ሲወስድ ጠቅላይ ናሙና ይባላል፡፡ በጥናቱ ከታቀፈው ትመህርት ቤት የተመረጡት ተማሪዎች 50 ናቸው፡፡

### 3.1.3 የመምህራን አመራረጥ

ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት ትምህርት ቤት በ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በአፍ መፍቻነት የምታስተምር መምህርት ብዛት አንድ ብቻ በመሆኗ በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተወስዳ ለቃለ መጠየቅ ተሳታፊ ተደርጋለች፡፡የመምህሯ አጠቃላይ መረጃ አንድ ብቻ መሆኗ እድሜዋ 40 ሲሆን የትምህርት ደረጃዋ በአማርኛ ድግሪ ያላት መሆኗ አገልግሎቷ 18 አመት ሲሆን እንደሁም በመሪ መምህርነት ደረጃ ላይ እንዳለች ያሳያል፡፡

## 3.2 መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋነኛ መሳሪያነት ያገለገሉት ሶስት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለተማሪዎች የሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆኑ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ደግሞ ለመምህሯ የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በዚህም የአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ በዓላማው ላይ የሰፈረውን የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ ምን ላይ እንደሚገኝ የሚመለስ ሲሆን የተማሪዎች ፅሁፍ መጠይቅ እና የመምህራን ቃለ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃዎች ይገኙበታል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

### 3.2.1 የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመዘን የሚሰጥ ፈተና

አንዱ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ፈተና ነው፡፡ ጥናቱም ሁለት አንብቦ መረዳት ፈተናዎች ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ አኳያ እንዲመጥኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል፡፡ ፈተናዎቹም ሲዘጋጁ በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው መረሀ ትምህረቱን መሰረት መማድረግ እና ለክፍለ ደረጃ ለሚጠበቀው ችሎታ እንዲመጥኑ ተደረገው ነው፡፡እንዲሁም በተዛማጅ ፅሁፍ ውስጥ የተለያዩ ምሁራን የገለጹትን መሰረት በማድረግ እና

በምዕራፍ ሁለት 2.6.1 ላይ የተገለጹትን መሰረታዊ ሀሳቦች እንዲያሟሉ ተደረገው ነው ።(አባሪ አንድን ይመልከቱ) ፈተናዎቹ ሁለት የሆኑበት ምክንያት በአንድ ፈተና ላይ ከመመስረት ይልቅ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፈተናዎችን መስጠት የጥናቱን ውጤት የበለጠ አስተማማኝ ስለሚያደረገው ነው (Madsen፣1983)::

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው አንበቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን ከሚያገለግሉት ጥያቄዎች መካከል ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉት የምርጫ፣ እውነት ሀሰት ፣ ክፍት ቦታዎችን መሙላት ፣ኣጫጭር መልስ የሚሹ ክፍት ጥያቄዎች ናቸው።በመሆኑም በዚህ ጥናት ወስጥም በተዘጋጁት ሁለት ፈተናዎች እነዚሁማለትም የምርጫና አጭር ምላሽ ክፍት ጥያቄዎች ተግባራዊ ሆነዋል ። እያንዳንዱ ፈተና አንድ አንድ ምንባብና ከምንባቡ የወጡ አምስት የምርጫ ጥያቄዎችና አምስት አጭር ምላሽ የሚሰጥባቸው ክፍት ጥያቄዎች ይዘዋል። በሁለቱ ፈተናዎች በአጠቃላይ 20(ሃያ) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ለተጠኚ ተማሪዎች ቀርቧል።

በተጨማሪም ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት የተሰጡትን ምንባቦች ማንበብና በሚገባ መረዳት የግድ በመሆኑ ተማሪዎቹ የቀደመ እውቀትን በመጠቀም በቀላሉ እንዳይመልሱ ጥንቃቄ ተደርጓል። ከዚያም ፈተናዎቹ ለተጠኒዎች ከመቅረባቸው በፊት በሁለት 2ኛ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ በማስተር ላይ በሚገኙ መምህራን እና በአንድ በደረጃው አማርኛ በማስተማር ላይ ባለች መምህርት እንዲገመገሙ በማድረግ እንዲሁም በአማካሪዬ ተገምግመው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል። ይህም የተዘጋጁ ፈተናዎች ለመፈተን የተፈለገውን ክሂል በትክክል ለመፈተን ከማስቻላቸው አኳያ ትክክለኛነታቸውን ለማወቅ ከመረዳቱም በላይ ግልጽነት የጎደላቸውንና የተወሰኑ አማራጭ መልሶችን ለማስተካከል አስችሏል። አጭር መላሽ ጥያቄዎችንም ውስን (በአርፍተ ነገር ወይም በሀረግ ደረጃ እና በመስመር) ተወስነው እንዲቀርቡ በተሰጠኝ አስተያየት መሰርት ተስተካክለው ቀርበዋል።

### 3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተግባራዊ የተደረገበት ዓላማ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እና የማንበብ ፍላጎታቸውን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታቸው እንዳይዳብር የሚያጋጥማቸውን ችግሮች፣ የንባብ ክሂላቸውን ለማዳበር በአካባቢያቸው በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ ፅሁፎችን የማግኘት እድላቸውን እና የክፍል

ውስጥ የንባብ ልምምዳቸው በተመለከተ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲቻል የፅሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቷል። (የጽሁፍ መጠይቁን አባሪ 2 ይመልከቱ) ።

የፅሁፍ መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን አጠቃላይ የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት መረጃ ለማግኘት እንዲረዳ የተዘጋጀ ነው። ሁለተኛው ክፍል በክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ላይ በማተኮር መረጃ ለማሰባሰብ ነው።ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የማንበብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸውን የማንበብ ፍላጎት መረጃ ለማሰባሰብና ከቃለመጠየቁ ከተገኙ መረጃዎች ጋር አስባጥሮ ለማየት እንዲያስችል ታስበው የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው።

### 3.2.3 ቃለ መጠየቅ

ለዚህ ጥናት ሌላው አጋዥ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የሆነው ለመምህሯ የሚቀርቡ ቃለ መጠየቅ ሲሆን ይህም በአጥኚዋ አስቀድመው በስርዓት የተዘጋጁና ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ይዟል። ጥያቄዎችም ከአጥኚዋ ጋር አብረው በሚሰሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሞያዎች ታይተው አስተያየት ተሰጥቶበት በተጨማሪም በአማካሪዬ ተገምግመው በተሰጠው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። በተደረገው ማሻሻያ መሰረት አንዳንድ ጥያቄዎች በሌሎች ተተክተዋል ፤ አዳዲስ ጥያቄዎችም ታክለዋል ። የቀረበውም በጥናቱ ተተኳሪ ለሆነችው አንድ መምህርት ነው። ይህም መምህረቷ በያዘችው ቀጠሮ መሰረት በዚሁ በተተኳሪው ትምህረት ቤት በግንቦት 15 /9/2015 ቃለመጠይቁ ይከናወናል ።(ለቃለ መጠይቁ የተዘጋጁ ጥያቄዎች አባሪ 3 ይመልከቱ)።

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናታዊ ስራ ውስጥ የጥናቱን አላማ ለማሳካት ከላይ በተገለጹት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ።መረጃው የተተነተነው አማካይ ውጤትን መሰረት በማድረግ በመቶኛ በመጠቀም ። እንዲሁም በሁለቱ አራሚዎች መካከል ያለውን የስተራረም ስምምነት ደረጃ አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ስታስቲክስ መረጃ ተግባር ላይ ውሏል።ከዚያም ፈተናዎቹ በሁለት በተላያዩ መምህራን ከታረሙ በኋላ በሁለቱም አራሚዎች ያገኝዋቸው ውጤት ከአስር ተመዘገቡ። ከዚያም በሁለቱ ፈተና ያገኙት ውጤት

ተደምሮ ለሁለት በማካፈል አማካይ ውጤት ተገኘ፡፡ ከዚያም ከየፈተናዎቹ ከእያንዳዳቸው የተገኘውን አማካይ የተጠኚዎች ውጤት እና ድግግሞሽ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት 2.9 በተለያዩ ምሁራን በተገለጸው ንድፍ ሃሳብ መሰረት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ መካከለኛ  ዝቅተኛ  በጣም ዝቅተኛ ተብለው ከዚያም በአጠቃላይ ተጠኚዎች የተገኘው ውጤት ድግግሞሽ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና መለኪያ ደረጃዎች ሰንጠረዥ በማስገባት ወደ መቶኛ ቀይሮ በማስቀመጥ በገለጻ ተተንትኗል፡፡ሌላው ለዚህ ጥናት በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው ለተማሪዎች የተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ተማሪዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጧቸው ምላሾችም ተደምረው በመቶኛ ስልት ከተቀመጠ በኂላ ማብራሪያ ተሰቶባቸዋል፡፡በመቀጠልም ለመምህር የቀረበ ቃለመጠይቅ ነው፡፡ከቃለመጠይቁ የተገኙት መረጃዎችን ከጽሁፍ መጠየቁ ጋር በአንድ ላይ እንደባህሪያቸው ተተንትነው ቀረበዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው በምስራቅ ቦረና ዞን በነጌሌ ቦረና ከተማ በተመረጠ የመንግስት ትምህርት ቤት አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የጥናቱ ክፍል በምዕራፍ ሶስት ላይ በዝርዝር በቀረቡት የመረጃ መሰብስቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ነው፡፡ በመጀመሪያ የጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በሆኑት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች እንደ ጥያቄዎቹ ቅደምተከተል ተሰብስበው ተተንትነዋል ፡፡እንዲሁም በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ በሆኑት ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅና ለመምህሯ ከቀረበው ቃለመጠየቅ አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች እንደየባህሪያቸው በማነጻጸሪያነት ቀርበዋል ፡፡እንዲሁም ፈተናዎቹ መረሃ ትምህርቱን መሰረት አድረገው የተዘጋጁ እና ምዕራፍ ሶስት 3.2.1 እንደተገለጸው በተለያዩ ባለሞያዎች እንዲገመግሙ ተደረገው አስተማማኝ እና ትክክለኛነታቸው ላይ በተደረገው ስምምነት ተጠኚዎች እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ከዚያም በምዕራፍ ሁለት 2.9 ላይ ባለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ መለኪያ መሰረት የአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈታኞች ከ 9-10 ውጤት ካስመዘገቡ ከፍተኛ ከ7-8 ውጤት ካስመዘገቡ መካከለኛ(በቂ)  ከ5-6 ካስመዘገቡ ደግሞ ዝቅተኛ  እና ከ5 በታች ውጤት ካስመዘገቡ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ተደርጎ ተወሰዷል ፡፡ ይህ ጥናትም ይህንን መነሻ በማድረግ የማንበብ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ፈተናዎች የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ንዑስ ክፍል በምዕራፍ ሶስት ላይ በዝርዝር በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃ ዎች የሚተነተኑበት ነው፡፡በመጀመሪያ የጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ በሆነው የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን በመቀጠልም በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም በጽሁፍ መጠየቅና በቃለመጠይቅ አማከኝነት የተገኙ መረጃዎች ጠቅለል ባለ መልክ ተተንትነው ይቀርባሉ፡፡

## 4.1.አንብቦ መረዳት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት አብይ አላማ 2015 በሾላ አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው የሚገኝበትን ደረጃ ማወቅ ነው፡፡በመሆኑም ለዚሁ አላማ መረጃ ለማግኘት ሲባል በጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑ ተማሪዎች ሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ተዘጋጅተው ተሰተዋል፡፡ እያንዳንዱ ፈተና አንድ ምንባብና ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ አምስት የምርጫ እንዲሁም አጭር ምላሽ የሚሹ አምስት ክፍት ቦታን የመሙላት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በመሆኑም ሁለቱ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች እያንዳንዳቸው አሰር አሰር ጥያቄዎች በድምሩ ሃያ ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡እንዲሁም ሁለቱ ፈተናዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ እና በጥናቱ ለተካተቱት ሀምሳ ተጠኚ ተማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡

በሁለቱም ፈተናዎች ለቀረቡ ሁሉም ጥያቄዎች አንድ አንድ ነጥብ ተሰጥቷቸው ታርመዋል፡፡ከዚያም ተማሪዎቹ በሁለቱም ፈተናዎች የገኙት ውጤት ከታወቀ በኋላ በምዕራፍ ሁለት ሰንጠረዥ አንድ ላይ በተገለጸው መሰረት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና  አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመመዘን የተለያዩ ምሁራን የተስማሙበት መስፈርት ውስጥ አስገብቶ ለመግለጽ ውጤቱ ከ 10 ተወስዷል፡፡  በአማካይ ያገኙት ውጤት በድግግሞሽ መጠን እና በመቶኛ ተሰልቶ በምድብ በተጠቃለለ የተፈታኞች አንብቦ የመረዳት ደረጃ በማስገባት ጠቅላይ አማካይ ውጤት ቀርቧል፡፡ በመሆኑም የተገኘውን አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት በመጠቀም ተጠኚዎች በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጽሁፎችን የማንበብ ተነሳሽነትኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን  ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡ይህም

የተከናወነው በምዕራፍ ሁለት ሰንጠረዥ አንድ ላይ የተለያዩ ሙሁራን በተስማሙበት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ መስፈርት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ውጤቱም በሰንጠረዥ ሁለት ላይ የተመለከተውን ይመስላል፡፡

## 4.2 የአጠቃላይ ተፈታኞች አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል ለጥናቱ በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት የሚገኙ ተጠኚዎች በሁለቱም የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች በአማካይ ያስመዘገቡትን ውጤት ለማየት ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎ በተመለከተው ሰንጠረዥ ተጠኚዎች በአንብቦ መረዳት ፈተናዎች በአማካይ ያገኙት ውጤት በድግግሞሽ መጠንና በመቶኛ ተሰልቶ በሁለቱም ምንባቦች ተለይቶ ቀርበዋል ፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡ በአራሚ 1 እና 2 ለተጠኚዎች ከቀረቡ አንብቦ የመረዳት መለኪያ ሁለት ፈተናዎች የተጠኚዎች አጠቃላይ እና የአማካይ ውጤት ድግግሞሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡**

| ፈተና አንድ ከ10 % | በአራሚ አንድ የተገኙ የተጠኚዎች | | በአራሚ ሁለት የተገኙ የተጠኚዎች | | አማካይ | | የፈተና ሁለት ከ10% የተገኘ ውጤት | በአራሚ አነድ የተገኘ የተጠኚዎች | | በአራሚ ሁለት የተገኘ የተጠኚዎቸ | | አማካይ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ | | ውጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ |
| 1 | - | - | - | - | - | - | 1- | - | - | - | - | - | - |
| 2 | 4 | 2 | 6 | 3 | 4 | 2 | 2 | 16 | 8 | 12 | 6 | 16 | 8 |
| 3 | 21 | 7 | 21 | 7 | 21 | 7 | 3 | 30 | 10 | 33 | 11 | 30 | 10 |
| 4 | 28 | 7 | 32 | 8 | 28 | 7 | 4 | 32 | 8 | 40 | 10 | 32 | 8 |
| 5 | 50 | 10 | 40 | 8 | 50 | 10 | 5 | 45 | 9 | 40 | 8 | 45 | 9 |
| 6 | 84 | 14 | 72 | 12 | 85 | 14 | 6 | 30 | 5 | 30 | 5 | 30 | 5 |
| 7 | 28 | 4 | 28 | 4 | 28 | 4 | 7 | 28 | 4 | 21 | 3 | 28 | 4 |
| 8 | 24 | 3 | 32 | 4 | 24 | 3 | 8 | 16 | 2 | 24 | 3 | 16 | 2 |
| 9 | 18 | 2 | 18 | 2 | 18 | 2 | 9 | 18 | 2 | 27 | 3 | 18 | 2 |
| 10 | 10 | 1 | 20 | 2 | 10 | 1 | 10 | 20 | 2 | 10 | 1 | 20 | 2 |
| | 267 | 50 | 269 | 50 | 268 | 50 | | 235 | 50 | 237 | 50 | 236 | 50 |
| | 5.34 | | 5.38 | | 5.36 | | | 4.7 | | 4.74 | | 4.72 | |

አጠቃላይ የውጤት ድምርን ለማገኘት እያንዳንዱ ከ10 የተመዘገበውን የፈተና ውጤት በተጠኝዎች ብዛት በማባዛትና ሁሉንም በአንድነት መደመር ማለትም (1x0)+(2x3) +(3x7)+(4x7) ---(9x2)+ (10x1)የተገኘ ነው፡፡

አማካይ ውጤቱን አጠቃላይ የውጤት ድምርን በተጠኝዎች ብዛት በማካፈል ማግኘት ይቻላል ድግግሞሽ ተማሪዎች ያግኙት የውጤት ተመሳሳይነት ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው የውጤት ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹን የወሰዱ ተጠኚዎች ብዛት 50 ናቸው ፡፡ከነዚህም 50 ተፈታኞች መካከል በአራሚ አንድና በአራሰሚ ሁለት ለተጠኝዎች ከቀረቡ አንብቦ የመረዳት መለኪያ ፈተናዎች የተገኙ አጠቃላይ ውጤት ድግግሞሽ እና የሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤት ደግግሞሽ ነው፡፡በዚህ መሰረት በአራሚ አንድ እና በአራሚ ሁለት የተገኙ አማካይ ውጤቶች በተከታታይ 5.34 ፣ 5.38 ነው፡፡ ይህም ከአስተራረምና ከውጤት አሰጣጥ አንጻር በአራሚዎቹ መካከል ከፍተኛ ስምምነት መኖሩን ያመለከታል፡፡በፈተና ሁለት ደግሞ በአራሚ አንድእና በአራሚ ሁለት የተገኘው አማካይ ውጤቶች 4.7 እና 4.74 ነው፡፡ ይህም በፈተና አንድ እንደተገለጸው በሁለቱም አራሚዎች መካከል ልዩነት አለመኖሩን ያመላክታል፡፡የአራሚ አንድ እና ሁለት የፈተና አማካይ ውጤት አጠቃላይ ድምር 268 ነው፡፡የአማካይ ውጤቱ አማካይ ውጤት 5.36 ነው፡፡የፈተና ሁለት የሁለቱ አራሚዎች አማካይ ውጤት ድምር 236 ሲሆን አማካይ ውጤቱ ደግሞ 4.72 ነው፡፡ይህም በፈተና አንድና በፈተና ሁለት መካከል ያለው አማካይ ውጤት በአራሚዎቹ ከፍተኛ ስምምነት እንዳለ ያሳያል፡፡ እንዲሁም በፈተና አንድ ና በፈተና ሁለት መካከል የውጤት ልዩነት አለመኖሩ የፈተናዎቹን አስተማማኝነት አመላክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡ የፈተና አንድ እና ሁለት ነጠላና አጠቃላይ አማካይ**

| ከ 10 የተገኘ ውጤት | የፈተና አንድ አማካይ | | የፈተናሁለት አማካይ | | የሁለቱ ፈተናዎች አማካይ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ | ውጤት | ድግግሞሽ |
| 1 | - | - | - | - | - | - |
| 2 | 4 | 2 | 16 | 8 | 16 | 8 |
| 3 | 21 | 7 | 30 | 10 | 15 | 5 |
| 4 | 28 | 7 | 32 | 8 | 32 | 8 |
| 5 | 50 | 10 | 45 | 9 | 50 | 10 |
| 6 | 85 | 14 | 30 | 5 | 48 | 8 |
| 7 | 28 | 4 | 28 | 4 | 28 | 4 |
| 8 | 24 | 3 | 16 | 2 | 24 | 3 |
| 9 | 18 | 2 | 18 | 2 | 18 | 2 |
| 10 | 10 | 1 | 20 | 2 | 20 | 2 |
| አጠቃላይ ድምር ውጤት | 268 | 50 | 236 | 50 | 251 | 50 |
| አማካይ ውጤት | 5.36 | | 4.72 | | 5.02 | |

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የውጤት ሠንጠርዥች መረዳት እንደሚቻለው በሁለትም አራሚዎች የተገኘው የፈተና ውጤቶች በጣም ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ማለትም ፈተና አንድ በአራሚ አንድ እና በአራሚ ሁለት የተገኘው አማካይ ውጤት ድግግሞሽ እና በፈተና ሁለት የተገኘው አማካይ የውጤት ድግግሞሽ ተደምረው ለሁለት በማካፈል 5.02 ጠቅላይ አማካይ የውጤት ድግግሞሽ ተገኝተዋል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት በምዕራፍ ሁለት እደተገለጸው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የራሱ የሆነ መለኪያ ስላለው ነው፡፡ ይህንንም ስሌት ለመስራት ጠቅላይ የአማካይ ውጤት ድግግሞሽ ስለሚስፈልግ ይህን ለማግኘት ሠንጠርዥ 3 ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከላይ በሠንጠርዥ 3 የተገኘው የተጠኚዎች ጠቅላይ

አማካይ ውጤት ድግግሞሽ በምዕራፍ ሁለት 2.9 እንደ ተገለጸው ( hughes 1995: Nuttall 1987 and Narayanas warumy 1995 ) በሚስማሙበት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ደረጃ መስፈርቶች በማስገባት እና በመቶኛ አስልቶ በማስቀመጥ የተማሪው አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ተገልጻል፡፡

### ሠንጠረዥ 4፡ በሁለት አራሚዎች የተገኘ በምድብ የተጠቃለለ የተፈታኞች አንብቦ የመረዳት ፈተና አጠቃላይ አማካይ ውጤት

| ምድብ | ደረጃ | የፈተና ውጤት | ድግግሞሽ | | ጥቅል ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | / 10% / | ብዛት | መቶኛ | |
| 1 | ከፍተኛ | 9-10 | 3 | 6 | 3 |
| 2 | መካከለኛ /በቂ/ | 7-8 | 7 | 14 | 10 |
| 3 | ዝቅተኛ | 5-4 | 24 | 48 | 34 |
| 4 | በጣም ዝቅተኛ | ከ5 በታች | 16 | 32 | 50 |

ሠንጠርዥ 4 የተመለከትነው በምድብ በተጠቃለለ በሁለቱም አራሚዎች የተገኘ የተፈታኞቹ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት 3(6%) ፣ መካከለኛ (በቂ) ውጤት ያስመዘገቡ 7(14%) ፣ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ 24(48%) እና በጣም ዝቀተኛ ውጤት ያስመዘገቡ 16(32%) ናቸው ፡፡ ከፍተኛ እና መካከለኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች 10(20%) ሲሆኑ ዝቅተኛ ና በጣም ዝቅተኛ ውጤት ያገኙት ደግሞ 40/80% ናቸው፡፡ ይህ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እደሚገኝ ያመለክታል፡፡

በአጣቃላይ የተጠኚዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስንመለከት በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲካሄድ ተማሪዎቹ ንባቡን ሲያካሄዱ ንባቡን ተሳሳትኩ አልተሳሳትኩ እያሉ ከመስጋት ውጪ ሲሳሳቱም መምህር እየተከተለ ከማስተካከል ባለፈ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲያዳብሩ ሲረዳቸው እዲሁም ተማሪዎቹም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሳደግ ሲጥሩ አይታይም ፡፡ስለዚህ የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲሰጥ ትኩረት ሊሰጠው እንደመገባ እንደዚሁም

ንባብ ላይ ብቻ ትኩረታቸው እንዳይሆን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ላይም ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የመለከታል ፡፡

## 4.3 ከፅሁፍ መጠይቅ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት የሚያግዙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የፅሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች ተሰራጭቶ እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት የፅሁፍ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ ተጠኚዎች ብዛት 50 ናቸው፡፡ይህም ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት አስችሏል ፡፡ በፅሁፍ መጠየቁ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች ከዚህ በታች በቀረቡ ሶስት ሠንጠርዥዎች ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኚዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች**

| የጥ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ |
| 1 | ከምንባብ የወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄችን ለመስራት ያለህ/ሽ ችሎታ | 3 | 6 | 9 | 18 | 16 | 32 | 12 | 24 | 10 | 20 |
| 4 | አንብቦ የመረዳት ችሎታህን/ሽን ለማዳበር የምታደርገው/ጊውጥረት ምን ያህል ነው | - | - | 4 | 8 | 8 | 16 | 24 | 48 | 14 | 28 |
| 3 | በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ምንም ሳልቸገር በፍጥነት አንብቤ እረዳለሁ | - | - | 20 | 40 | 18 | 36 | 7 | 14 | 5 | 10 |
| 15 | አንብቦ የመረዳት ችሎታህ/ሽ ምን ያህል ነው | - | - | 10 | 20 | 26 | 52 | 11 | 22 | 3 | 6 |
| 2 | አንድን ታሪክ ካነበብክ በኋላ ርዕሰ ጉዳዩንየሚመለከቱ ጥያቄዎችን በትክክል መመለስ እችላለሁ | - | - | 14 | 28 | 27 | 54 | 9 | 18 | - | - |

ሠንጠርዥ 5 ላይ እደተመለከተው የተጠኝዎችን የአማርኛ ቋንቋ እውቀት በአማርኛ የቀረቡ ጹሁፎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ አምስት ጥያቄዎች ቀርበዋል ። የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማወቅ ታስቦ ለቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ 16(32 በመቶ) ተጠኚዎች ከምንባቡ የውጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ለመስራት መካከለኛ እንደሆኑ የገለፁ ሲሆን 12 (24 በመቶ) የሆኑት ዝቅተኛ እና 10(20 በመቶ) ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆኑ ገልጸዋል። 9(18 በመቶ) ደግሞ ከፍተኛ እና 3(6በመቶ) በጣም ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በሠንጠረዡ በሰፈረው መረጃ ማየት ተችሏል ።ከነዚህም መረጃዎች የአብዛኛዎቹ ተጠኚዎች ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመስራት ያላቸው ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

እንደዚሁም በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ከምንበብ የወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በተማሪዎች የሚሰሩ ናቸው። ነገር ግን አብዛኛዎቹ አንብቦ የመረዳት ጥየቄዎች የቤተ ስራ ወይም የክፍል ሰራ ይሰጣቸው እና ከመምህራቸው ጋር በጋራ በቃለቸው ስለሚሰሯቸው ከምንባብ ለወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመስራት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው ። በተጨማሪም የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ እጥረት ከተማሪው ቁጥር ጋር አለመጣጣም ተገቢ የክፍል ቁጥጥር አለማድረግ ከምንባብ ለወጡ አንበቦ የመረደት ጥየቄዎችን በክፈል ውስጥ ለአለመሰራታቸው ምክንያቶቸ ሆነው ተጠቀሰዋል።

አንብቦ የመረዳት ችሎተህን/ሽ ለማዳበር የምታደርገው /ጊው ጥረት ምን ያህል ነው የሚለውን ይመለከታል። 4(8 በመቶ ) ከፍተኛ የሚሉትን ሲመርጡ 8(16 በመቶ )መካከለኛ እንደሆኑ የጠቆሙ ሲሆን 24 (48 በመቶ) ዝቅተኛ እና 14(28 በመቶ )በጣም ዝቅተኛ እንደሆኑ ያመለክታል።እነዚህ መረጃዎች አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያግዙ ተጨማሪ በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን በአከባቢያቸው የማያገኙና የማያነቡ መሆኑን ይጠቁማሉ ።እንዲሁም በቃል መጠየቁ ላይ መምህርቷ ከሰጡት አስተያየት ጋር ማለትም ስለንባብ ጥቅም አለማወቃቸው በተጨማሪም ቤተ መጽሐፍት አለመኖሩ በትምህርት ቤት ብቻ ሣይሆን በአከባቢያቸው ላይም አለመኖሩ ነው ሲሉ ከሰጡ ምላሽ ጋር የሚጣጣም ነው።

በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን ምንም ሳልቸገር በፍጥንት አንብቤ እረዳለሁ የሚለውን ምን ያህል አንብበው እንደሚረዱ በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ ለተጠየቀው ተጠኚዎች ከሰጡት ምላሽ በአማርኛ የተጻፈ ማንኛውንም ጽሁፎች አንብበው መረዳት እንደሚችሉ የገለፁት 20(40 በመቶ)ብቻ

ናቸው ፡፡አብዛኛዎቹ በፍጥነት አንብበው እንደሚረዱ የገለጹት 18 (36 በመቶ) መካከለኛ እና 7(14 በመቶ ) ዝቅተኛ እንደሆኑ የገለጹ ሲሆን እንዲሁም 5(10 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ በፍጥነት አንብቦ መረዳት የማይችሉ እንደሆኑ ያሳወቁ ናቸው ፡፡ ይህ በተጠኚዎች የተሰጠው ምላሽ በፍጥነት አንብበው እንረዳለን ካሉት በልጦ ይታያል ይህም በርከት ያሉ ተማሪዎች በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፍዎችን በፍጥነት አንብበው መልዕክቱን ለመረዳት እንደሚያዳግታቸው ይጠቁማል ፡፡እንዲሁም ከተሰጠው አማራጭ ውጪ በራሳቸው መልስ የሰጡት ደጋግመው ማንበብ እንዳለባቸው ብዙ ጊዜ ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው አንብበው በፍጥነት መረዳት የማችሉ እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ይህም መምህሯ በቃለ መጠየቁ ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያለቸው ተነሳሽነት አናሳ እንደሆነ ማለትም በክፍል ውስጥ ለሚደረግ ለንባብ ትምህርት በራስ ተነሳሽነት ማንበብ እንደማይፈልጉ ከጠቆሙት ጋር ይመስሰላል፡፡

ተማሪዎች በአማርኛ የቀረቡ ምንባቦችን ምን ያህል አንብበው እንደሚረዱ በጥያቄ ቁጥር 15 ላይ ለተጠየቀው ተጠኚዎች ከሰጡት ምላሽ በሁሉም ምንባቦች ውስጥ ያሉትን መልዕክቶች አንብበው መረዳት እንደሚችሉ የገለጹት 10 (20 በመቶ) ብቻ ናቸው፡፡አብዛኞቹ አንብቦ በመረዳት ችሎታቸው በመካከለኛ እንደሚገኙ የገለጹት ደግሞ 26 (52 በመቶ) ናቸው ፡፡ አንብቦ በመረዳት ከቀረቡት ምንባቦች አንዳንዶቹን አንብበው መልዕክቱን እንደሚረዱ ያሳወቁና አንዳንዶቹ እንደማይረዱ ያሳውቁት 11(22 በመቶ )እና 3(6 በመቶ) በድምሩ 14 (28 በመቶ ) ተጠኚዎች ናቸው ፡፡ይህም በተጠኚዎች የተሰጠው ምላሽ በሁሉም ምንባቦች እንረዳለን ካሉት በልጦ ይታያል፡፡

ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ችሎታ አንብበው መልዕክቱን ለመረዳት እደሚቸገሩ መረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም መምህሯ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው ብለው ከሰጡት አስተያየት ጋር የሚስማማ ነው፡፡

አንድን ታሪክ ካነበብክ /ሽ በኂላ ርዕሰ ጉዳዩን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በትክክል መመለስ እንደሚችሉና እንደማይቻሉ በጥያቄ 2 ላይ ለተጠየቀው ተጠኚዎች በሰሰጡት ምላሽ 14(28 በመቶ )የሚሆኑት በትክክል መመለስ እንደሚችሉ የገለጹ ሲሆን 27(54 በመቶ ) መካከለኛ እና 9(18 በመቶ )ዝቅተኛ መመለስ የሚችሉ ናቸው ፡፡ይህም አብዛኛውን ጊዜ በመምህራን ስለሚተገበር ማለትም መምህር ያነባል አንዴ ወይም ሁለቴ ተማሪዎቹም ያዳምጣሉ ከዚያም ጥያቄዎችን አብረው በጋራ ይሰራሉ፡፡ ስለዘህ ለጥያቄው ከተሰጡት መልሶች መረዳት

የሚቻለው ተማሪዎች አንድን ምንባብ አንብበው  በዚያ ምንባብ ዙሪያ ለሚጠየቁት ጥያቄ ለመመለስ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ  6፡ የተጠኚዎችን በአማርኛ የቀረቡ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ**

| የጥያቄ ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በብዛት | በመቶ | በብዛት | በመቶ | በብዛት | በመቶ | በብዛት | በመቶ | በብዛት | በመቶ |
| 5 | ከመምህሬ ድጋፍ ውጪ ማንበብ እችላለሁ | 6 | 12 | 12 | 24 | 28 | 56 | 8 | 16 | 3 | 6 |
| 8 | በምንባብ ወቅጥ ለሚየጋጥሙ አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ ትርጉም የመስጠት ችሎታ | 2 | 4 | 8 | 16 | 17 | 34 | 19 | 38 | 4 | 8 |
| 9 | በልምምድ ወቅት ሲቀርብልን የነበሩት ምንባቦች አንብቦ ለመረዳት ብዙም አስቸጋሪ አልነበሩም | 2 | 4 | 7 | 14 | 25 | 50 | 11 | 22 | 5 | 10 |
| 10 | ከምንባብ ውስጥ ዋናዋና እና ዝርዝር ሀሳቦች የመለየት ችሎታህ /ሽ | - | - | 4 | 8 | 24 | 48 | 14 | 28 | 8 | 16 |
| 11 | ከምንባብ በኃላ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ | 5 | 10 | 7 | 14 | 22 | 44 | 13 | 26 | 3 | 6 |

ሠንጥረዥ 6 የተጠኚዎችን በአማርኛ የቀረቡ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ  እ በአማርኛ የቀረቡ ጽሁፎች የማንበብ ፍላጎት ና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማወቅ አምስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በአማርኛ የቀረቡ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት ችሎታውን ለማወቅ የቀረበው ጥያቄ 5 8(16 በመቶ) ዝቅተኛ እና 3 (6 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ከመምህራቸው ድጋፍ ውጪ ማንበብ እንደማይፈልጉ ወይም እንደማይችሉ የገለጹ ሲሆን

28(56 በመቶ) መካከለኛ ከመምህራቸው ድጋፍ ውጪ ማንበብ የሚችሉ 12(24 በመቶ) ከፍተኛ እና 6(12 በመቶ) በጣም ከፍተኛ ከመምህራቸው ድጋፍ ውጪ የማንበብ ፍላጎት እንዳለቸው የገለጹ ናቸው፡፡በቃለመጠይቁ መምህሯ ተጠኚዎችን ምንም አይነት ጽሁፎችን ከመምህራቸው ድጋፍ ውጪ ማንበብ እንደማይፈልጉ በንባብ ጊዜ እንኳን የተለያዩ ስራዎችን እንደሚሰሩ ጠቁመዋል፡፡

በምንባብ ወቅት ለሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ ትርጉም የመስጠት ችሎታ ለተጠየቀው ጥያቄ 8 19(38 በመቶ) ዝቅተኛ እና 4(8 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ችሎታ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ 17 (34 በመቶ) መካከለኛ 8 (16 በመቶ) ከፍተኛ እና 2(4 በመቶ) በጣም ከፍተኛ ችሎታ ወይም ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ናቸው፡፡ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው በምንባብ ወቅት ለሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ ትርጉም የመስጠት ችሎታቸው ወይም ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡ከነዚህም መረዳት የሚቻለው ለቃላት ከአገባባቸው አኳያ ትርጉም የመስጠት ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ በመምህር ስለሚከናወን ተማሪዎችም ከመምህራቸው ጋር መስራት እንጂ እራሳቸው ለመስራት ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ነው ፡፡

በልምምድ ወቅት ሲቀርቡልን የነበሩት ምንባቦች አንብቦ ለመረዳት ብዙም አስቸገሪ አልነበረም ለሚለው ጥያቄ 9 11(22 በመቶ )ዝቅተኛ እና 5(10 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ አንብቦ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነባቸው ናቸው፡፡ 25 (50 በመቶ) መካከለኛ  7 (14 በመቶ) ከፍተኛ እና 2(4 በመቶ) በጣም ከፍተኛ አንብቦ ለመረዳት ያልተቸገሩ እንደሆኑ ያሳወቁ ሲሆኑ ለጥያቄው ከተሰጠው ምላሽ ስንረዳ ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ካልተቸገሩ ይልቅ ምንባቡን አንብበው ለመረዳት የተቸገሩት ቁጥር ከፍተኛ ስለሆነ ከዚህም የምንረዳው በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ ምንባቦች ግልጽነት የጎደላቸው አንብቦ ለመረዳት የሚያስቸግሩ እንዲሁም የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑን የጠቆሙ ናቸው፡፡

ከምንባብ ውስጥ ዋና ዋና እና ዝርዝር ሃሳቦችን የመለየት ችሎታህ/ሽ ምን ያህል ነውየሚለውን ለማወቅ በቀረበው ጥጣቄ 10 14(28 በመቶ) ዝቅተኛ እና 8 (16 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ የመለየት ችሎታ እንዳላቸው የገለጹ ሲሆኑ 24 (48 በመቶ) መካከለኛ 4(8በመቶ) ከፍተኛ የመለየት ችሎታ እንዳላቸው ያሳወቁ ናቸው፡፡ከዚህም የምንረዳው ተማሪዎቹ አንድን ምንባብ አንብቦ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ እንዲሁም ችሎታ የሌላቸው መሆኑን ከቃለ መጠይቁ መረዳት ተችሏል፡፡

ከምንባብ በኋላ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ ለሚለው ጥያቄ 11 13(26 በመቶ) ዝቅተኛ 3(6 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ከምንባብ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎች መጠየቅ እንደማይችሉ ያሳወቁ ሲሆን 22(44 በመቶ) መካከለኛ 7 (14 በመቶ) ከፍተኛ እና 5(10 በመቶ) በጣም ከፍተኛ ከምንባብ በኋላ መጠየቅ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ከምንባብ በኋላ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡

ባጠቃላይ በሰንጠረዥ 6 ከሰፈሩት መረጃዎች የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ስንመለከት ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተገንዝበናል እንዲሁም የንባብ ትምህርት በራሱ ችግር እንዳለበት በአማርኛ የመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ግልጽነት የጎደላቸው እንደሆኑ አንብቦ ለመረዳትም ተማሪዎች እንደሚቸገሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የተጠኚዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚኖራውን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ያላቸውን የማንበብ ፍልጎት የተመለከቱ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በፁሁፍ መጠየቁ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ለጥያቄዎቹ በተጠኙዎች የተሰጡ ምላሾች በሠንጠርዥ 7 ቀርበው ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡ የተጠኚዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎትን በተመለከተ ከቀርቡት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ | ብዛት | በመቶ |
| 6 | በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል ያለህ/ሽ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው | 4 | 8 | 11 | 22 | 22 | 44 | 11 | 22 | 2 | 4 |
| 12 | በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎትህ/ሽ ምን ያህል ነው | 5 | 10 | 10 | 20 | 13 | 26 | 20 | 40 | 2 | 4 |
| 14 | በክፍል ውስጥ አንድ ምንባብ ከተነበበ በኂላ በምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ላይ ከጓደኞችህ/ሽ ጋር በቡድን በመሆን ለመወያየትያለህ /ሽ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው | 3 | 6 | 7 | 14 | 19 | 38 | 18 | 36 | 3 | 6 |
| 13 | በክፍል ውስጥ በሚደረጉ የንባብ ልምምዶች የመሳተፍ ፍላጎትህ/ሽ ምን ያህል ነው | 1 | 2 | 6 | 12 | 13 | 26 | 24 | 48 | 6 | 12 |
| 7 | አንድን ምንባብ ካነበክ /ሽ በኂላ ስላነበብከው/ሽው መልስህ/መልስሽ መናገር ትችላልህ/ሽ | - | - | 21 | 42 | 12 | 24 | 17 | 34 | - | - |

ሰንጠርዥ 7 ላይ እንደተመለከተው አምስቱም ጥያቄዎች ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎት ለማወቅ ሲባል የቀረቡ ናቸው፡፡በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህረት ሲሰጥ ለመከታተል ያላቸውን ተነሳሽነት በተመለከተ በጥያቄ 6 ለቀረበው 22(44 በመቶ) ተጠኚዎች መካከለኛ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት እንዳላቸው ገልጸዋል ፡፡ 11(22 በመቶ) ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው እና 2(4 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ 4(8 በመቶ )ደግሞ በጣም ከፍተኛ እና 11(22 በመቶ) ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው መሆኑን በሰንጠርዥ በሰፈረው መረጃ ማየት

ተችሏል፡፡ከነዚህም መረጃዎች አብዛኞቹ ተጠኚዎች የማንበብ ተነሳሽነታቸውና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡እንዲሁም በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ትኩረት ሰጥተው ከመከታተል ይልቅ የተለያዩ የቤት ስራዎችን መስራት  የራሳቸውን ወሬዎች ማውራት ሰ  ጨዋታዎችን ሲተገብሩ ይስተዋላሉ እንጂ የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የማንበብ ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱ ተግባራትን ሲፈጽሙ አይስተዋሉም ፡፡ይህም ከአንብቦ መረዳት ችሎታን መለኪያ ፈተና ከተማሪዎች ውጤት ጋር የማይስማማ ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ስለዚህም የማንበብ ፍላጎት ማነስ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ፅሁፎችን የማንበብ ፍላጎት በተመለከተ በጥያቄ 12 ላይ ለቀረበው 20(40 በመቶ) ዝቅተኛ እና2 (4 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ፍላጎት ሰእንዳላቸው ገልጸዋል፡፡13 (26 በመቶ) መካከለኛ ፈላጎት እንዳላቸው የጠቆሙ ሲሆን 10(20 በመቶ) ከፍተኛ እና 5(10 በመቶ) ደግሞ በጣም ከፍተኛ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት እንዳለቸው ጠቁመዋል ፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል ፡፡ስለዚህ በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎትን ሲታይ ከመምህር ትዛዝም እንደሚጠብቁ ወይም አንብቡ ተብለው እንጂ በራስ ተነሳሽነት ማንበብ እንደሚፈልጉ መምህሯ ከሰጡት አስተያየት መረዳት ተችሏል ፡፡

በክፍል ውስጥ አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ በምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ላይ ከጓደኞችህ /ሽ ጋር በቡድን ለመወያየት ያላቸው ተነሳሽነት በተመለከተ በጥያቄ 14 ላይ  ለቀረበው 10(20 በመቶ) ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው ገልጸዋል ፡፡19 (38 በመቶ) መካከለኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው ሲገልጽ 18 (36 በመቶ) ዝቅተና 3(6 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ከነዚህም መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ምንባብ ከተነበበ በኋላ ፍሬ ሃሳብ ላይ አብዛኛውን ተማሪዎች በቡድን ለመወያየት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡

በክፍል ውስጥ በሚደረጉ የንባብ ልምምዶችን የመሳተፍ በተመለከተ በጥያቄ 13 ለቀረበው 24(48 በመቶ) ዝቅተኛ ፍሰላጎት እንዳላቸው 13( (26 በመቶ) ማከለኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጻል፡፡ለዚህ ምክንያት የልምምዱ  ሂደት በመማሪያ መጽሐፍ እጥረት  የተነሳ ውሰን በመሆኑ የመሳተፍ እድሉ አናሳ ነው፡፡ 7(14 በመቶ) ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ፍላጎት

እንዳላቸው አመላክተዋል፡፡ ከነዚህ መረጃዎች  የንባብ ልምምድ በክፍል ውስጥ መውስን እና የመማሪያ መጽሐፍ ለተማሪዎች በበቂ ሁኔታ አለመድረሱ  የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ ነው፡፡ እንዲሁም በቃለ መጠየቁ መምህሯ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያመለከቱ ሲሆን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

አንድ ምንባብ ካነበበክ/ሽ በኋላ ስላነበብከው/ሽው መልሰህ/ሽ መናገር መቻል አለመቻላቸውን ለተጠየቁ ጥያቄ 7ላይ ለቀረበው 21(42 በመቶ) ከፍተኛ መልሰው መናገር እንደሚችሉ ሲገሊጹ 12(24 በመቶ) መከከለኛ እንሰደሆኑ የገለጹ ናቸው፡፡ 17( 34 በመቶ) ዝቅተኛ እንደሆኑና ምንም መልስ መናገር እንደማይችሉ ደጋግመው ማንበብ እንዳለባቸው የገለጹ ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደምንችለው ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው መልሰው መናገር የሚችሉ 42 በመቶ ከፍተኛ እና 24በመቶ መካከለኛ መናገር የሚችሉ መሆናቸውን ነው 34 በመቶዎቹ ግን መልሰው መናገር እንደማይችሉ መገንዘብ ተችሏል፡

በአጠቃላይ በዚህ ሠንጠረዥ እንደተመለከተው በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል 22(44 በመቶ) መካከለኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው 11(22 በመቶ) ዝቅተኛ እና 2(4 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው የገለጹ ሲሆኑ 4(8 በቶ) ደግሞ በጣም ከፍተኛ እና 11(22 በመቶ) ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ናቸው ፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት  ሲሰጥ ለመከታተል ያለቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት 20(40 በመቶ) ዝቅተኛ እና 2(4 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡13 (26 በመቶ) መካከለኛ ፍላጎት እንደዳላቸው የጠቆሙ ሲሆን 10 (20 በመቶ) ከፍተኛ እና 5(10 በመቶ) ደግሞ በጣም ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ናቸው፡፡ይህንንም ስንመለከት በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት ካላቸው ፍላጎት የሌላቸው በልጠው ይታያል ፡፡ ስለዚህ ማንኛወም በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ለላይ እንዳለ ያሳያል ፡፡

በክፍል ውስጥ አንድ ምንባብ ከተነበበ ባኋላ በምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ላይ በቡድን ለመወያየት 10(20 በመቶ) ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው እና 19(38 በመቶ) መካከለኛ ተነሳሽነት 18(36 በመቶ) ዝቅተኛና3 (6 በመቶ) በጣም ዝቅተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው

ገልፀዋል፡፡ከዚህም መረዳት የሚቻለው በምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ዙሪያ ለመወያየት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡

በክፍል ውስጥ በሚደረጉ የንባብ ልምምዶችን የመሳተፍ ፍላጎት 24(48 በመቶ) ዝቅተኛ ፍላጎት 13(26 በመቶ) መካከለኛ ፍላጎት እንዳላቸው እና 7(14 በመቶ) በጣም ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው አመልክቷል፡፡መምህሯ በቃለመጠይቁ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚደረጉ የንባብ ልምምዶች ትኩተረት እንደማይሰጡ በፍላጎት ማንበብ እንደማይፈልጉ እንዲውም በግዴታ በመምህር ድጋፍ እንደሚያነቡ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዳይዳብር ተጽዕኖ ማሳደሩን ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቹ የማንበብ ተነሳሽነታቸውና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ስንመለከት በዚህ ጥናት ከታቀፉት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚሆኑት የማንበብ ተነሳሽነታቸውና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሳባተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማወቅ  የተካሄደ ነው፡፡ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት በአማርኛ ቋንቋ  አፋቸውን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር ፣ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ  ፣ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ያላቸው  የማንበብ ፍላጎትን  መመርመር የሚሉ ናቸው፡፡

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና ከተማ ስምንት የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበት እና አፈ ፊት ተማሪዎች የሚማሩበት አንድ ትምህርት ቤት ብቻ በመሆኑ ይህ ትምህርት ቤት በአላማ ተኮር ናሙና ዘዴ ተወስዷል፡፡ እሱም ሾላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ተጠኚዎቹም የዚሁ ትምህርት ቤት 50 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡እነሱም ሁሉም በጠቅላይ ናሙና ዘዴ  ተወስደዋል፡፡በዚሁ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ ሰባተኛ ክፍል የምታስተምር አንድ መምህርት ብቻ በመሆኗ እሷም በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተወስዳ ጥናቱ ተካሄዷል፡፡

በዚህ መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የዋለው ለተማሪዎች የቀረበ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ሲሆን ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅና ለመምህር የቀረበ ቃለ መጠይቅ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ስለሆነም የጥናቱ ገላጭ ምርመር ዘዴን በዋናነት በመጠቀም እንዲሁም መጠናዊ የምርምር ዘዴን በአጋዥነት በመጠቀም በመረጃ  መሰብሰብያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጤት በገለጻ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ለተማሪዎች ከቀረቡት ሁለት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች 6% ከፍተኛ ውጤት 14% መካከለኛ ውጤት ፣ 80% ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ውጤት

ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ስለዚህ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመላክታል ፡፡

የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን መፈተሽ የሚለውን ለማወቅ ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ እና ለመምህር ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሲታይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከምንባብ የወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ለመስራት ብቃታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ለማዳበር በአማርኛ የተጻፉ ጽሁፎችን በአከባቢያቸው የማያገኙና የማያነቡ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም በቃለ መጠይቁ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን የመሰራት ልምድ እንደሌላቸው ብዙን ጊዜ ከመምህራቸው ጋር በጋራ የመስራት ልምድ እንዳላቸው የጠቆሙ ሲሆን እንደዚሁም በትምህርት ቤታቸው፣በአከባቢያቸው ቤተ -መጽሐፍት ባለመኖሩ ምክንያት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የማዳበር በቃታቸው ዝቅተኛ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ስለዚህ የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎት የሚለውን ለማወቅ ለተማሪዎች ከቀረቡት የጽሁፈ መጠየቅና ለመምህር ከቀረበው ቃለ መጠየቅ የተገኘው መረጃ ተማሮዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳብር ያላቸውን የማንበብ ፍላጎት ዝቅተኛ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ይህም በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል ፍላጎት አለመኖር አብዛኛውን ጊዜ ንባብ የሚከናወነው በመምህር መሆን ተማሪዎችም በዚህ አጋጣሚ የተለያዩ የቤት ስራዎችን መስራት ፣ማውራት እንጂ ትኩረት ሰጥተው አለመከታተል እንዲሁም በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎት በተመለከተ ተማሪዎቹ ለማንበብ ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ንባብ በመምህር እንጂ በተማሪው አልፎ አልፎ መሆን ይህ እንዲሆን ያደረገው ከተማሪው ቁጥር ጋር ተያይዞ ክፍለ ጊዜ ያለመብቃት የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል ሲሉ በቃለመጠየቁ ገልጸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረደት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው የማንበብ ፍላጎት እንዳይዳብር ያደርጋል፡፡ስለዚህም የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህን ጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ አጥኚዋ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማደበር ይጠቅማሉ ያለቻቸውን አስታያየቶች ከዚህ በታች እንደሚከተለው አቅርባለች ፡፡

- የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሳደግ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ትኩረት ተሰቶት በአግባቡ ቢተገበር የተሻለ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል
- ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ጥረት ቢያደርጉ
- መምህራን የማንበብ ተነሳሽነትን ሊጨምሩ የሚችሉ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ ቢያነቡላቸው እንዲያነቡ ቢጋብዙ
- መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ፣በፊትም ሆነ በኋላ የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ከፍ ሲል አንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ከፍ እንደሚል ተገንዝበው የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ቢያሳድጉ መልካም ነው፡፡
- የመማሪያ መጽሐፍት በበቂ ሁኔታ ተማሪዎቹ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎቹ ደረጃ የሚመጥኑና የአንብቦ መረደት ጥያቄዎችን ለመስራት የሚያስችሉ መማሪያ መጽሐፍት በበቂ መጠን ለሁሉም የሚዳርስበት ሁኔታ ቢመቻች
- ለተማሪዎቹ የሚቀርበው የንባብ ትምህርት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ብቻ የተወሰነ እንዳይሆን በትምህርት ቤቱ ሆነ በከተማው ቤተመጽሐፍት እንዲኖር ቢደረግ በተቻለ መጠን ለተማሪዎቹ የሚመጥኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ወቅታዊ የሆኑ የህትመት ውጤቶች ቢሟሉና ለተማሪዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ቢደረግ
- የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ሰፋ ያለ ጥናትና ምርምር ቢደረግ ችግሩ ሊቃለል ይችላል ፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች

ሒሩት ካሳዬ። (2008) ። በምዕራብ ሐረርጌ ዞን በሂርና ከተማ በተመረጡ የመንግስት ት/ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፍተሻ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኤም ኤ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)

አስቴር አስራት። (2010) ። የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ ፤አምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ፊትሿል። በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ) ።

ማረው አለሙ። (1998) የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሰርካለም ይገረሙ። (2010) ። አእምሮአዊ የማንበብ ስልቶች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም ኤ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)

አለም እሸቱ። (1991)። «ንባብ አንብቦ መረዳት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ።»አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ጥናት ተቋም ለአስረኛ አመት የቋንቋ ጥናት ስንፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ።

ተስፋዬ ሸዋዬ። (1986)። አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር። አዲስ አበባት.መ.ማ.ድ።

ያለው እንዳወቅ። (2009) ። የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

እንዲሪስ አባይ ። (2009)። በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ በስድስተኛ ክፍል ፈትሿል።

በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክተሬት የዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ) ።

ዘውዱ መብሬ። (2008) ። ሚናለዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፈ ፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በ7ኛ ክፍል ፈትሿል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም ኤ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ (ያልታተመ)

Bachman .LF. (1990). <u>Fundamental Considertions in Language testing</u> .Oxford: Oxford University press.

Brown, H, D. (1994) .Teaching by Principles on Interactive Approach to Language Pedagogy: New york.Prentice Hall

Carrell, p 1983 “Three Components of Background Knowledge in Reading comprehension” languge learning journal, vol 33/2:pp.183-228

Davey, Beth. (1987). “Relation Butwen Word Knowledge and Comprehension: Generallaztion across Task and Readers. “ Journal of Educational Research, 80 (3).pp 179-183.

Davies.F. (1995) .Introducing Reading. England: Penguin Books Ltd.

Dubin .F .and David B. (1991). In Celece-murcia.m. (Ed) Teaching English as Second or Foreign Language. Boston: Heinle and Heine Publishers.

Dubin.F. (1989). “The Odd Couple: Reading and Vocabulary” In Engish Language Teaching. Oxford: Oxford University Press Col. 43/4pp283-287/

Grant.W. (1990). The Case for Authentic Assessement Research: And Evaluation: Vol.2. Article2.

Grellet.F. (1981) Developing reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer.J.(1991). The Practice of Engilsh Language Teaching .London: Longman.

Heaton. J.B. (1991).Writing English Language Tests. Newyork: Longman Inc.

Hughes, A. (1995). Testing for Language Teachers .Cambrigde Cambridged Univeristy Press.

Madsen. H. S (1983) .Techniques in Testing. Newyork: Oxford University Press.

Narayanas Warmy .K.R. (1975). “The Measraement of Reading Ability” In English Language Teaching” Oxford University press. Vol.29/2 pp 143 - 150.

Nuttall.C. (1982). Teaching Reading Skills For in a Foreign Language .London: Henemann Educational books.

Nuttall.C. (1987). Teaching Reading Skills For in a Foreign Language .London: Henemann Educational books.

____________ (2000). Teaching Reading Skills For in a Foreign Language .London:Henemann Educational books.

Sheng.He. (2000). A Cognitive model for Teaching Reading Comprehension: ”the English forum. 38. Pp, 12 – 15.

Smith .F. (1985) Reading Cambridge: Cambridge University press.

-------------- (1989) Reading. Cambridge: Cambridge University press.

Stavens, A. and Brenda.o. (1993). “Assessing EFL Reading Comprehension: “The Course of Ethiopia learners. System. 21(4). PP. 481-491.

Ur.P. (1996). A Course in Language Teaching Practice and Thoery. Cambridged Univeristy press.

Weir .C.J. (1990). Communicative Language Testing .London: Pretice Hall International Ltd.

Williams.E. (1984). Reading in The Language Class Room .London: Macmillan publishers Ltd.

Williams, E. (1990). Reading in Language Class Room.London: Macmillan publishers.

Wigfield, A. and Guthrite, J. (1997).Reletions of Children's Motivation for Reading to the Amount Breadth of Their Reading. Journal of Educational Psychology, 89,470-437.

Guthrie, J.T. & Wigfield, A. (2000) . Engagement and Motivation in Reding.In M.L. Kamil P.B Mosenthal, P.D pearson, and Barr (Eds) , Handbook of Reading Research (Vol.III, pp.403-22) Mahwah, NJ.Lawrence Erlbaum Associates.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# አንብቦ የመረዳት ምንባቦች ከነጥያቄዎቻቸው

አንብቦ የመረዳት ፈተና

ፈተና አንድ

ስም ከነአባት

ፆታ ________________

ዕድሜ ______________________

አጠቃላይ መግለጫ፡- የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መፈተሸ ነው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተሰጡት መመሪያዎች መሰረት መልስ/ሽ፡፡

**ምንባብ አንድ**

ዛሬ የማወጋችሁ ስመ ገናና ዝነኛና ታዋቂ ስለሆነው ልጄ ስለ ጥቁር አባይ ነው፡፡"እ!" ብዬ አምጬ የምወልደው እኔ ነኝ፡፡ ግን የእናት ወግ አሳይቶኝ አያውቅም፡፡ ጥሎን ወደ ባእድ ሀገር ይፈተለካል፡፡ ከምስራቅ አፍሪካ ተነስቶ ሰሜን አፍሪካ ሜዴትራንያ ባሀር ያድራል፡፡ እሩቅ ተጓዥ በመሆኑ፣ብዙዎች ማደሪያ ቢስ ይበሉት እንጂ ምን የመሰለ ማደሪያ አለው፡፡

ልጄ ጥቁር አባይ ፣ከጊሻባይ ተነስቶ፣ ጣና ሀይቅን አቋርጦ ፣ከራሴ ወንዞች ያገኘውን ውሃ ይዞ ወደ ባእድ ሀገር እብስ ይላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለብዙ ሺህ ዓመታት ለፍቼ፣ደክሜና የሰው ፊት እየገረፈኝ ለልጆቼና ለልጅ ልጆቼ እንዲሆን ያስቀመጥኩትን ጥሪት ጥርግርግ አድርጎ እያግበሰበሰ ባልደፈርም ባይነት ስሜት የጀግና ፉከራ እየፎከረና እየሸለለ፣ገደል ለገደል እየተገለባበጠ፣መልከ መልካምነቱን ብቻ እያሳየኝ ፣ዓይኔ ከእርሱ ጋር ክርትት ሲል ጥሎኝ

ጥርግ ይላል ፡፡አጨካከኑን ያየ ዳግም መለስ ብሎ ላያየኝና የልጅ ወጉን ላያሳየኝ ቃለ መሀላ ያለበት ሳይመስለው አይቀርም፡፡

እጅግ የሚገርመው ደግሞ ገና ከቤቱ ወጣ ሲል ጉዞው ሁሉ አደባባይ ለአደባባይ መሆኑ ነው፡፡ አመሉን ማሳመሩ ነው መሰለኝ! ከምንጩ ተነስቶ 1400ኪ.ሜ ያህል ከተጓዘ በኋላ ካርቱም አቅራቢያ ሲደርስ ጉዞውን ኡጋንዳና ደቡብ ሱዳንን በዋና ከተማዋ በጁባ ላይ አቋርጦ ከደቡባዊ አቅጣጫ ወደ ሰሜን ከሚፈሰው ከነጭ አባይ ጋር ያደርጋል፡፡ከዚህ በኋላ  ሁለቱም ጥቁርና ነጭ የሚለውን የግል መጠሪያ ትተው አባይ ይባላሉ፡፡ ታድያ ነጭ አባይ ከጥቁር አባይ ጋር እስከሚገናኝ ድረስ ያለው የውሃ መጠን በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም ፣የጥቁር አባይን ያህል የእናቱን ንብረት ጥርግርግ አድርጎ ለማውጣት የሚያስችል አቅም የለውም ፤ ቁጥብ ነው፡፡

በልጄ በኩል ብዙ ውሃ ለአባይ እኔ ልገብር እንጂ ፣ከእኔ ይልቅ አባይን ጥሩ አድርገው የተጠቀሙበት ሱዳንና ግብጽ ናቸው፡፡ለበርካታ አመታት ለመስኖ ፣ለሀይል ማመንጫ፣ለቱሪስት መስህብነትና ለዓሳ ምርት እየተገለግሉበት ነው፡፡ በተለይ ግብጻውያንን ፣ጥቁር አባይ ከጥንት ጀምሮ በምግብ እህል እራሳቸውን እንዲችሉ አደርጓቸዋል፡፡ ግብጾች ለምን በአባይ ተጠቅመው አደጉ የሚል አንጀት የለኝም፡፡እድገታቸው የእኔም እድገት ነውና፡፡ሆኖም እጄ አመድ አፋሽ መሆኑ ያንገበግበኛል፡፡ልጆቼ በተለያዩ ጊዚያት በተከሰቱ ድርቆች መጠቃታቸውና  በአለም ላይ የርሀብና የድህነት ተምሳሌት መሆናቸው በብርቱ ይሰማኛል፡፡ «የአባይን ልጅ ወሃ ጠማው» ማለት ይሄ አደለም? ገጣሚውስ ቢሆን ፣«… የእጅን ሰጥቶ ጦም አዳሪ ፤ጥጋብ ሰጥቶ ተበዳሪ …» ያለው ምኑን ይመስላችኋል?

አሁን ግን የልጄ እሩቅ አዳሪነት ይብቃ ብዬ ተነስቻለሁ !ልጆቼ እስከ መቼ የእጃችሁን እየሰጣችሁ በድህነት ትኖራላችሁ? እስከ መቼ የርሀብና የድርቅ ተምሳሌት እየተባላችሁ ትጠራላችሁ?እስከ መቼ ለዳቦ ስንዴ ትለምናላችሁ እስከመቼ ደህነት ሲነሳ አንገታችሁን ትደፋላችሁ እንደጀመራችትሁት አቅም ያለው በጉልበቱ ፣ሀብት ያለው በገንዘቡ፣የተማረው ደግሞ በእውቀቱ ተረዳዱና በርትታችሁ ለወንድማችሁ ጎጆ ቀልሱለት፡፡ልጄ ቅረብ እያደሩ መንዝን ከለመደ ፣እየጠራረገ የሚወስደውን የምድሬን በረከት እዚሁ ስለሚዘረግፍላችሁ ደህነትና ርሀብ ያበቃላቸዋል ፡፡እናንተም እንደሌሎች ወንድም ህዝቦች  የሲሳዩ ተጋሪ ትሆናላችሁ፡፡ የአገራችሁን ሰርዶ በሀገራችሁ በሬ ትነቅሉና በምድሬ በረከት ትጠግባላችሁ፡፡እስከዚያው ደህና ሰንብቱልኝ …

ምንጭ ፦ኑሩ ኢብራሂም 2008 ገጽ 343

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ በምንባቡ መሰረት መልስ የያዘውን ሆሄ በማክበብ መልሱ፡

1. «ጥቁር አባይ ባልደፈርም ባይነት ስሜት የጀግና ፉከራ እየፎከረ ፣እያቅራራና እየሸለለ ይፈተለካል፡፡ » የሚለው አገላለጽ ጥቁር አባይ ---------መሆኑን ይገልጻል፡፡

ሀ/ከፍተኛ ድምጽ አያሰማ የሚሄድለ/ከጀግኖች ሀገር ፈልቆ የሚፈስ

ሐ/በጣም ብዙ ውሃ ይዞ የሚጓዝ መ/ በማን ይነካኛል ስሜት የሚጓዝ

2. በምንባቡ ውስጥ የጥቁር አባይ እናት -------፡፡

ሀ/ ስለጥቁር አባይ ለልጆቿ በለገሰችው ምክር ተሰፋ አድርጋለች

ለ/ ስለ ጥቁር አባይ ያላት ሀሳብ ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ አይችልም

ሐ/ በልጇ ድርጊት በጣም ተበሳጭታለችመ/ በልጇ ሁኔታ በጣም ተስፋ ቆርጣለች

3.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምንብቡ ዋና ሀሳብ በአጭሩ ይገልጻል፡፡

ሀ/ ጥቁር አባይን በመገደብ የሲሳዩን ተጋሪ መሆን ይቻላል ፡፡

ለ/ሌሎች ጠግበው እየበሉ ኢትዮጵያዊያን በቂ ስንዴ ማምረት ተስኖአቸዋል፡፡

ሐ/ በጥቁር አባይ ጥሩ አድርገው የተጠቀሙት ሱዳንና ግብጽ ናቸው፡፡

መ/ጥቁር አባይ ከሀገሩ ወጣ ስል አመሉን ያሳምራል፡፡

4.በምንባቡ ውስት የጥቁር አባይ እናት ምን አይነት ስሜት ይነበብባታል?

ሀ /የኩራት ለ/የቁጭት ሐ/የቅናት መ /የምቀኝነት

5.በምንባቡ መጨረሻለወንድማችሁ"ጎጆ ቀልሱለት "ምንን ያመለክታል?

ሀ/ጥቁር አባይ መጠለያ እንዲሰራለት ለ/ጥቁር አባይ የሚጠራርገው አፈር መኖር እንደሌለበት

ሐ/ ጥቁር አባይ መገደብ እንዳለበት መ/ ጥቁር አባይ ከሀገር እንዳይወጣ መገደብ እንዳለበት

II.ከዚህ በታች ምንባቡን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ አምስት ጥያቄዎዎ ቀርበዋል፡፡ ከእያንዳንዱ ጥያቄ ስር በተተውት ክፍት ቦታዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት ጥቁር አባይ ማረፍያ ቢያገኝ ምን ሊሆን ይችላል____________________________________________________

2. ነጭ አባይ ቁጥብ ነው የተባለው ለምንድነው?

____________________________________________________________

3. የልጄ እሩቅ አዳሪነት ይብቃ ብዬ ተነስቻለሁ! ሲል ምን ማለቱ ነው ?

________________________________________________________

4. በልጄ በኩል ብዙ ውሃ ለአባይ እኔ ልገብር እንጂ ሲል ማንን ማለቱ ነው?

________________________________________________________

5. .የዚህ ምንባብ ርዕስ ምን ሊሆን ይችላል?

____________________________________________________________________

## ምንባብ ሁለት

## ለተሻለ ውጤት በርትታችሁ አጥኑ !

ራስን ለቆሙበት ወይም ለተሰለፉበት ዓላማና ግብ አዘጋጅቶ መብቃት መቻል ብልህነት ነው፡፡ ትናንትን በዛሬ ዓይን አስታውሶ በጎ ተግባር የተከናወነበትን ጠብቆ ለማራመድ መሞከሩን ስንደገግፍ ጌዜን ደግሞ በስርዓት በመጠቀም ካለ መቻል የተነሳ በመደጋገም ከስህተት ማጥ ለመዘፈቅ ከመጋበዝ ከሕይወት ባለልምዶች መማር ለመታረምና ለመስተካከል መነሳሳቱ ተመራጭነት አለው፡፡አንድ ተክል አድጎ ለፍሬ እስከሚበቃ በቂ ክትትልና ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ ሁሉ ሕፃናት በጨቅላነታቸው ፣ወጣቶች በትኩስ አእምሮአቸውና ጉልበታቸው …ወዘተ ተኮትኩተው አድገው ለነገ ሰው እንዲበቁ መገራት አለባቸው፡፡

በአንድ ወቅት አንድ ምሁር «እውቀት በእርጅና ዘመን መጠለያ በመሆኑ ገና በወጣትነት ዕድሜ መተከል ያለበት መሰረት ነው፡፡» እንዳሉት በመልካም ሥነ -ምግባር መወጠንና ውጥኑም ስኬታማ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

በትምህርት ዓለም መንዝ ላይ ሚገኙ ሁሉ አላማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ጥረት ባሻገር ከህብረተሰቡ ወጥተው የቀሰሙትንና የሸመቱትን ዕውቀት በተግባር ለማስመስከር ዕለት ተዕለት ተግቶ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ባያጡትም በዚህ የጋራ ሙያዊ ተግባር በተለይም ወጣት ተማሪዎች የእውቀት አምባ የእድገትና የስልጣኔ መሰረት ከሆነው የትምህርት ማዕዳቸው መልካም ስነ-ምግባርን ቀስመው የቀሰሙትን በስርዓት ወደ ህብረተሰቡ ዘልቀው ለማድረስ እንዲበቁ በመማሩ መድረክ ከሚገኙት የዕውቀት አባቶቻቸው የሚማሩት እንዳለ ይሰማናል፡፡

የመልካም ስነ-ምግባር ምልልስ ከሁሉ ሁሉ ከአጉል ሱስ የራቀ በመጤ ባህል ያልተጠመቀ በባህሪው ራሱን በምሳሌነት አቁሞ በርቱዕ አንደበቱ የተሳሳተን ለመመለስ ያጠፋን ለማረም አስተምሮም ሆነ መክሮ መልካሙን መንገድ አሳይቶ መልካም የስራን ለበለጠ ውጤት እንዲበቃ ድጋፍ የሚሰጥ ያለውን ሰጥቶ ተቀባይ የሚያጣ በተማሪዎች ዘንድም ተቀዳጅነትና ከበሬታ የማይሰጠው ዓይነት ነው፡፡(ከክልላዊ ፈተና የተወሰደ )

I. የሚከተሉትን ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎች በአማራጭነት ከተሰጡት መልሶች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ብቻ በማክበብ መልሱ፡፡

1. አንድ ተክልና ሕፃናት የሚመሳሰሉት በምንድን ነው?

ሀ/አንድ ተክል አድጎ ለፍሬ እስኪበቃ በቂ ክትትልና ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚገባ በመሆኑ

ለ/ ሕፃናት በጨቅላነታቸው ፣ወጣቶች በትኩስ አምሮአቸውና ጉልበታቸው …ተኮትኩተው ማደግ የሚገባቸው በመሆኑ

ሐ/ ለነገው መልካም ፍሬያማነት ሁለቱም ተንከባካቢ ባለቤት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ

መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል

2. የጠፋን ማረም የተሳሳተን መመለስ የማን ተግባር ይመስላል?

ሀ/የወላጆች ለ/ የመምህራን ያላሳለሰ ጥረት

ሐ/ የዕድሜ እኩዮች ተግባር መ/የማንኛውም ህብረተሰብ ተግባር

3. መልካም ስነ- ምግባር እሴቶችን የሚገልፀው አንቀፅ------ ነው

ሀ/ አራተኛ ለ/ ሁለተኛ ሐ/ ሶስተኛ መ/ አንደኛ

4. የዕውቀት አባቶቻቸው ማለቱ

ሀ/ወላጅ አባቶችን መግለጹ ነው ለ/ ተንከባካቢያቸውን መግለጹ ነው

ሐ/መምህሮቻቸውን መግለጹ ነው መ/ ማህበረሰቡን መግለጹ ነው

5. መልካም ስነ -ምግባር የሚለው አባባል -------------ይመለከታል

ሀ/ ጨዋነትን ለ/ ደንብንና ስነ-ስርዐት አክባሪነትን ሐ/ መልካም አርዓያ መሆንን መ/ ሁሉም

I.ከዚህ በታች ምንባቡን መሰረት ያደረጉ አምስት ጥያቄዎች ቀርበዋል ከእያንዳዱ

ጥያቄ ስር በተተወው ክፍት ቦታዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ

1.የትምህርት ማእዳቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?

__________________________________________________________

2.በምንባቡ መሰርት በመጤ ባህል ያልተጠመቀ ሲል ምን ለማለት ነው?

______________________________________________________________________________

3. ከስህተት ማጥ ውስጥ መዘፈቅ ከሚለው አባባል የምንረዳው

ምንድ

ነው?______________________________________________________________

4. ለጥሩ ስብእና እንዲበቁ መገራት አለባቸው የሚለውን አገላለጽ በአንድ አረፍተ ነገር ግለጽ/ጪ

5. «እውቀት በእርጅና ዘመን መጠለያ በመሆኑ ገና በወጣትነት እድሜ መተከል የለበት መሰረት ነው» የተባለው ለምንድነው ____________________________________

# አባሪ 2

# የጽሑፍ መጠይቅ

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በ2015 በነጌሌ ቦረና ከተማ ሾላ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ እና አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ ነው፡፡ የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ፤ በኦሮሚያ ክልል በምስረቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና ከተማ በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍ ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለማስትሬት ዲግሪ ማሟያ ለሚደረግ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የምትሰጡት መረጃ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ሲሆን ሚስጥራዊነቱም የተጠበቀ ነው፡፡

የእናንተ ትክክለኛ ምላሽ የጥናቱ ውጤት ተቀባይት እንዲኖረው ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የጽሑፍ መጠይቁን በአግባቡ በመሙላትና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ለጥነቱ መሳካት የበኩላችሁን አስተዋጽዖ እንድታደርጉልኝ እጠይቃለሁ፡፡

ስለትብብራችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ጾታ

ዕድሜ

ማሳሰቢያ

1. መጠይቁ ላይ ሥም መጻፍ አያስፈልግም

2. መጠይቁን በየግላችሁ መሙላት ይኖርባችኋል፡፡ከሌላ ሰው ጋር የምትሞሉ ከሆነ በእናንተ ምላሽ ላይ የተሞረኮዘውጥናት ውጤት ሊዛባ

## መመሪያ

ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች እያንዳዳቸው አምስት አማራጮች አሏቸው እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ በማንበብ ከፊትለፊት ከቀረቡት አምስት አማራጮች መካከል

1.በጣም ከፍተኛ 2 .ከፍተኛ 3. መካከለኛ 4 .ዝቅተኛ 5 .በጣም ዝቅተኛ የሚሉት ሲሆኑ ትክክለኛ ነው የምትሉትን በጥያቄው ፊለፊት ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በመልሱ አቅጣጫ የ "X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመስራት ያለህ/ሽ ችሎታ | | | | | |
| 2 | አንድን ታሪክ ካነበብኩ በኃላ ርዕስ ጉዳዩን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በትክክል መመለስ እችላለሁ | | | | | |
| 3 | በአማርኛ የተጻፉ ጹሁፎችን ምንም ሳልቸገር በፍጥነት አንብቤ እረዳለሁ | | | | | |
| 4 | አንብቦ የመረዳት ችሎታህን /ሽን ለማዳበር የምታደርገው /ጊው ጥረት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 5 | ከመምህሬ ድጋፍ ውጪ ማንበብ እችላለሁ | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል ያለህ/ሽ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 7 | አንድን ምንባብ ካነበብክ/ሽ በኃላ ስላነበብከው/ሽው መልሰህ/ሽህ ትችላለህ/ሽህ | | | | | |
| 8 | በምንባብ ወቅት ለሚያግጥሙ አዳዲስ ቃላት ከአገባባቸው አኳያ ትርጉም የመስጠት ቸሎታ | | | | | |
| 9 | በልምምድ ወቅት ሲቀርቡልን የነበሩት ምንባቦች አንብቦ ለመረዳት ብዙም አስቸጋሪ አልነበሩም | | | | | |
| 10 | ከምንባብ ውስጥ ዋና ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን የመለየት ችሎታህ/ሽ | | | | | |
| 11 | ከምንባብ በኃላ ጥያቄ መጠየቅ እችላለሁ | | | | | |
| 12 | በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሁፎችን የማንበብ ፍላጎትህ /ሽ ምን ያህል ነው | | | | | |
| 13 | በክፍል ውስጥ በሚደረጉ የንባብ ልምምዶች የመሳተፍ ፍላጎትህ/ሽ ምን ያህል ነው | | | | | |
| 14 | በክፍል ውስጥ አንድ ምንባብ ከተነበበ በኃላ በምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ላይ ከጓደኞችህ /ሽ ጋር በቡድን በመሆን ለመወያየት የለህ /ሽ ተነሳሽነት ምን ያህል ነው | | | | | |
| 15 | አንብቦ የመረዳት ችሎታህ /ሽ ምን ያህል ነው | | | | | |

## አባሪ 3

## ቃለ መጠይቅ

ይህ ቃለ መጠይቅ በነጌሌ ቦረና ከተማ ሸላ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

ውድ መምህራን የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋአፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን በነጌሌ ቦረና ከተማ በ7ኛክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ሲሆን ይህንንም ለመገምገምና የመፍትሔ ሀሳብ ለመሰንዘር የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ እርስዎ ይህንን ቃለመጠይቅ እንዲመልሱ የተፈለገበትም ለጥናቱ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ክፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ የተሻለ እንዲሆን ጥያቄዎቹን በግልጽነት እንዲመልሱልን በትህትና እጠይቃለሁ ስለትብብርዎ በቅድሚያ አመሰግናለሁ

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1. ጾታ______________________________
2. የትምህርት ደረጃ ________________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ __________________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት _____________________
5. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ _______________________
6. የአገልሎት ዘመን__________________________

## ክፍል ሁለት

1.አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ምን ይመስላ?

2. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ጽሑፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውስ ምን ይመስላል?

3.የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጫወተው ሚና?

4.በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የማረዳት ፍላጎት የሚያነሳሱ ናቸው ብለው ያስባሉ?

5.ከመማርያ መጽሀፍ ውጪ እንዲያነቡ ይገፏፏቸዋል?

6.በአማርኛ ክፍለ ግዜ ተማሪዎች የንብብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

7. የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

8.ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት?

# ማረጋገጫ

“በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፍተሻ፤ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ቦረና ዞን ነጌሌ ቦረና በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት በማንኛውም አካል ያልተሰራና ወጥ የራሴ ሥራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትን በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስናፍቅሽ አዱኛ

___________________

መስከረም 2016